# የ'ሙዳ' ስርዓተከበራ ክወና እና ትዕምርታዊ ውክልና፤ በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነቅርስ

ሰሎሞን ተሾመ[1]


## አጠቃሎ

የዚህ ጥናት አቢይ ዓላማ በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነቅርስ የሙዳ ስርዓተከበራ የአከዋወን ቅደምተከተልና ክወናው ያለውን ትዕምርታዊ ውክልና መተንተን ነው፡፡ የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነቅርስ በባሌ ዞን ጎሎልቻ ወረዳ፣ አናጂና ቀበሌ የሚገኝና በአስራ ሁለተኛው መቶ ክፍለዘመን እንደተመሰረተ የሚነገር ኃይማኖታዊ ስፍራ ነው፡፡ የሙዳ በዓላት በመካነቅርሱ በአመት ሁለት ጊዜ የሚከበሩ የመታሰቢያ ስርዓተከበራዎች ናቸው፡፡ ጥናቱ ይዘታዊ ምርምር የጥናት አይነትን የተከተለ ነው፡፡ ለጥናቱም ምልከታና ቃለመጠይቅ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ተግባራዊ ተደርገዋል፡፡ የተሰበሰቡ መረጃዎች ያላቸውን ትርጉም በፍከራ ለማሳየት የክወና እና ትዕምርታዊ ንድፈሃሳቦችን መሰረት በማድረግ የተዘጋጀ ጥናት ነው፡፡ በሙዳ በዓል ወቅት የሚከወኑ ስርዓተከበራዎች በዋሬ ስፍራ፣ በከራ ጉዶ እና በቅጽር ግቢው ውስጥ እንዲሁም በአይናገኜ ገደል የሚከወኑ እንደሆኑ ጥናቱ ያሳያል፡፡ በሙዳ በዓላት ወቅት የሚከወኑ ስርዓተከበራዎች ለመንፈሳዊ ተጓዦች መንፈሳዊ እሴትን፣ የመንፈስ ለውጥን፣ የምሉዕነት ስሜትንና እርካታን የሚያጎናጽፉ እንደሆኑ ጥናቱ ያሳያል፡፡ የሙዳ ስርዓተከበራዎች ከማህበራዊና ሀይማኖታዊ ዋጋ አንጻር ልዩ ስፍራ የሚሰጣቸው ክወናዎች እንደሆኑ ጥናቱ አሳይቷል፡፡ ስርዓተከበራዎቹም በቅደምተከተላዊ ስርዓት፣ በተደጋጋሚና በመደበኛነት የሚከወኑ ጠቃሚ ድርጊቶችና ሕዝባዊ ሁነቶች ናቸው፡፡ የሙዳ ስርዓተከበራዎች የመንፈሳዊ ተጓዦችን፣ የአማኞችንና የከዋኞችን መንፈሳዊ፣ አዕምሯዊና ማህበራዊ ደረጃን ከፍ በማድረግ ከመንፈሳዊ ሀይሎች ጋር ግንኙነት ለመመስረት እንደሚረዳ ጥናቱ ያሳያል፡፡ ስርዓተከበራዎቹ የማህበረሰቡን ማንነት ለመፍጠር፣ ለመጠበቅ፣ እውቅና ለመስጠት ዋና መሰረት እንደሆኑ እንዲሁም የእርስበርስ ተግባቦት የሚፈጥሩ መሆናቸውን ጥናቱ አሳይቷል፡፡


*ቁልፍ ቃላት፤* ሙዳ፣ ስርዓተከበራ፣ ክወና፣ ትዕምርት

---

[1] ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ፣ኢትዮጵያ; ኢሜል፦ solodaw@yahoo.com

# የጥናቱ ዳራ

በአገራችን በተለያዩ አካባቢዎች መንፈሳዊ ጉዞ (Piligrimage) የሚካሄድባቸው ቦታዎች አሉ፡፡ በአገራችን የተለያዩ ቦታዎች የእስልምና፣ የክርስትና እና የሀገር በቀል ሀይማኖት ተከታዮች ያላቸውን የዘርና የሀይማኖት ድንበር በማለፍ በጋራ የሚያመልኳቸው መንፈሳዊ ቦታዎችና የሚፈጽሟቸው መንፈሳዊ ስርዓተከበራዎች (Rituals) መኖራቸውን Pankhurst (1994) ይገልጻል፡፡ ይህ አይነት የኃይማኖትና የባህል ውሕደት ከሚስተዋልባቸው የአገራችን መንፈሳዊ ቦታዎች መካከል አንዱ የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነቅርስ (Shrine) ነው (Pankhurst, 1994)፡፡

የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነቅርስ በ12ኛው መቶ ክፍለዘመን እንደተመሰረተ የሚነገር ኃይማኖታዊና ታሪካዊ ስፍራ ነው፡፡ መካነቅርሱ በኦሮሚያ ክልል፣ በባሌ ዞን፣ በጎሎልቻ ወረዳ በአናጂና ቀበሌ ይገኛል፡፡ የአናጂና ቀበሌ ከአዲስ አበባ በደቡብ ምስራቅ አቅጣጫ በ610 ኪሎ ሜትር ርቀት እንዲሁም ከባሌ ዞን ዋና ከተማ ሮቤ ደግሞ በ180 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ይገኛል፡፡ ስፍራው ስያሜውን ያገኘው በፈጣሪ የተመረጡና ታላቅ የሀይማኖት አባት እንደሆኑ በሚታመነውና መካነቅርሱን በመሰረቱት በሼኽ ሁሴን ሼኽ ኢብራሂም ስም ነው፡፡

በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የ'ሙዳ' በዓላት በዓመት ሁለት ጊዜ ይከበራሉ፡፡ 'ሙዳ' የሚለው ቃል ኦሮምኛ ነው፡፡ በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነቅርስ ሙዳ የሚለው ቃል በዓመት ሁለት ጊዜ የሚከበሩ በዓላትን፣ በበዓላቱ ወቅት የሚከወኑ ስርዓተከበራዎችን፣ ወደ ስፍራው የሚደረግ መንፈሳዊ ጉዞን እንዲሁም ወደ ስፍራው መንፈሳዊ ጉዞ የሚያደርግን ተጓዥ የሚገልጽ ነው፡፡

በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነቅርስ የሚከበሩ ሁለት የሙዳ በዓላት 'ኢድ-አል አድሃ (አረፋ)' እና 'ዛህራ ገልገላ ጎበና' በሚሉ ስያሜዎች ይታወቃሉ፡፡ በሁለቱም የሙዳ በዓላት እያንዳንዳቸው እስከአስር ቀናት የሚሸፍኑ ደማቅ መንፈሳዊ በዓላት ናቸው፡፡ በሙዳ በዓላት ወቅት የሚከወኑ የተለያዩ ስርዓተከበራዎች አሉ፡፡ እነዚህን ስርዓተከበራዎች የሙዳ በዓል ከመድረሱ በፊት፣ በሙዳ በዓላት ወቅት እና ከሙዳ በዓል በኋላ የሚከወኑ ናቸው፡፡ የዚህ ጥናት ትኩረት በሙዳ በዓል ወቅት የሚከወኑ ስርዓተከበራዎች ላይ ነው፡፡

በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ የእስልምና፣ የክርስትና፣ የዋቄፈና እና የሌሎች ሀይማኖቶች ተከታዮች፣ የተለያየ ብሔር ተወላጆች እንዲሁም

የውጪ አገር ዜጎች በጋራ አምልኮ ይፈጽማሉ፡፡ በዓመት ሁለት ጊዜ በሚከበሩ የሙዳ በዓላት ላይም በርካታ ቁጥር ያላቸው መንፈሳዊ ተጓዦች ወደ ስፍራው ይመጣሉ፡፡ በሙዳ በዓላት ወቅትም ከ500,000 (አምስት መቶ ሺህ) በላይ አማኞች በዓመት ሁለት ጊዜ ወደ ስፍራው እንደሚመጡ ይገመታል፡፡

ይህ ሀይማኖታዊ ስፍራ በርካታ ቁጥር ያለው ህዝብ ለአምልኮ የሚሄድበት በመሆኑም ይመስላል Braukämper (1984, p. 773) መካነቅርሱን "የሰሜን ምስራቅ አፍሪካ መካ" በሚል ይገልጸዋል፡፡ ከኢትዮጵያ የተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች ወደ መካነቅርሱ ስለሚሄዱ Eliyas (2002, p. 19) "ትንሿ ኢትዮጵያ" ብሎ ገልጾታል፡፡ እነዚህ አገላለጾች እንዳሉ ሆነው የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነቅርስ ከኢትዮጵያዊያን ውጪ ያሉ ሕዝቦችን፣ ከእስልምና ውጪ ያሉ የሌሎች ኃይማኖት ተከታዮችን ጭምር በአንድ የሚያገናኝ በመሆኑ "ትንሿ ዓለም" በሚል ሊገለጽ ይችላል፡፡

የዚህ ጥናት አቢይ ዓላማ በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነቅርስ የሙዳ ስርዓተከበራ አከዋወን እና ትዕምርት መተንተን ነው፡፡ ጥናቱም፤ በሙዳ በዓላት ወቅት የሚከወኑ ስርዓተከበራዎች ምን ምን ናቸው? ስርዓተከበራዎቹ ያላቸው ቅደምተከተላዊ ክወና ምንድን ነው? ስርዓተከበራዎቹ ያላቸው ትዕምርታዊ ውክልና ምንድን ነው? ለሚሉ የምርምር ጥያቄዎች መልስ የሚሰጥ ነው፡፡

## ጽንሰ ሐሳባዊ እና ንድፈሃሳባዊ ዳሰሳ

የስርዓተከበራ ጽንሰሀሳብ በጣም ሰፊ፣ ውስብስብ፣ ተለዋዋጭና በሰው ልጅ የታሪክና የባህል ጥናት ውስጥ በጣም ልዩ ስፍራ የሚሰጠው እንደሆነ Salamone (2004) እና ሰሎሞን (2007 ዓ.ም) ይገልጻሉ፡፡ የስርዓተከበራን ምንነት በተመለከተ የተለያዩ አጥኚዎች የተለያዩ ብያኔዎችን አስፍረዋል፡፡ ምሁራኑ ስርዓተከበራን ሲበይኑ በዋናነት ከሁለት ሰፋፊ ርዕሰጉዳዮች አንጻር ነው፡፡ እነሱም ስርዓተከበራን ከቅርጽ (Form) እና ከአገልግሎት (Function) አንጻር ናቸው፡፡ Rappaport (1999, p. 24) "ስርዓተከበራ በአብዛኛው የማይቀያየር፣ መደበኛ የድርጊት ቅደም ተከተልና የከዋኞች ፈጠራ የማይታከልበት ነው" በማለት ይገልጻል፡፡ ይህ ብያኔ ስርዓተከበራን ከቅርጽ አንጻር የሚገልጽ ነው፡፡

Eriksen (2001, p. 215) "ስርዓተከበራዎች በህግ የታቀፉ ሕዝባዊ ሁነቶች ሲሆኑ፣ በአንድ ወይም በሌላ መንገድ በመሬት ያለ አካልና በመንፈሳዊ ነገር መካከል ግንኙነት መፍጠሪያ መንገድ ናቸው" በማለት ይገልጻል፡፡ Cooke and Macy (2005, p. 21) "ስርዓተከበራ የባህልን ጥልቅ እሴት ማሳየት ብቻ ሳይሆን ባህልን የመፍጠር፣ የመጠበቅና እውቅና

የመስጠት ሚና አለው፡፡” በማለት ይገልጻሉ፡፡ እነዚህ ሁለት ብያኔዎች ደግሞ ስርዓተከበራን ከአገልግሎት አንጻር የሚገልጹ ናቸው፡፡ በሌላ በኩል Firth (1967, p. 12) “ስርዓተከበራ እንደመደበኛና ሂደታዊ የትዕምርቶች ስብስብ የሚወሰድ ሲሆን፣ የማህበራዊ ተግባቦት ምልክት (Code) ነው” በማለት ስርዓተከበራን ከቅርጽና ከአገልግሎት አንጻር ይበይነዋል፡፡

ከእነዚህ ብያኔዎች በመነሳት ስርዓተከበራዎች አንድ ማህበረሰብ ያለውን ባህል መነሻ በማድረግ ከማህበራዊና ሀይማኖታዊ ዋጋ አንጻር ልዩ ስፍራ የሚሰጣቸውን ክወናዎች በቅደምተከተላዊ ስርዓት፣ በተደጋጋሚና በመደበኛነት የሚከውናቸው ጠቃሚ ድርጊቶችና ሕዝባዊ ሁነቶች ናቸው፡፡ ስርዓተከበራዎቹ የከዋኞቹን መንፈሳዊ፣ አዕምሯዊና ማህበራዊ ደረጃን ከፍ በማድረግ ከመንፈሳዊ ሀይሎች ጋር ግንኙነት ለመፍጠር፣ ባህልን ለመፍጠር፣ ለመጠበቅና እውቅና ለመስጠት እንደሚያገለግሉ መረዳት እንችላለን፡፡

የስርዓተከበራ አይነቶች በርካታ ናቸው (Bell, 1977)፡፡ ከእነዚህ የስርዓተከበራ አይነቶች መካከል በድሬ ሼኽ ሁሴን የሙዳ በዓላት ወቅት የሚከወኑ ስርዓተከበራዎች የጊዜ ሰሌዳዊ ስርዓቶች (Calendrical rites) ስር ሊመደቡ የሚችሉ ናቸው፡፡ የጊዜ ሰሌዳዊ ስርዓቶች በጊዜ የተገደቡ፣ የሚከወኑበት ወቅት የታወቀ፣ ከተፈጥሯዊ የወቅቶች ሁኔታና የማህበረሰቡ ሕይወት ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡ የጊዜ ሰሌዳዊ ስርዓቶች ወቅታዊ (Seasonal) እና የመታሰቢያ (Commemorative) ስርዓተከበራዎች በሚል በሁለት እንደሚመደቡ Bell (1977) ትገልጻለች።

Bell (1977, p. 105) የመታሰቢያ ስርዓተከበራን ምንነት ስታብራራ፣ “የመታሰቢያ ስርዓተከበራ በአንድ አገር ወይም ማህበረሰብ ላይ የተከሰቱ ልዩ ታሪካዊ ገጠመኞችን ለማሰብ ወይም በአንድ ኃይማኖት አስተምህሮ ውስጥ የኃይማኖቱ ዋና ምሰሶ የሆኑ ቅዱሳን የተወለዱበትን፣ ልዩ ተዓምራት የፈጸሙበትን ወይም ያረፉበትን ቀን ለማሰብ በሚል የሚከወኑ ናቸው” ትላለች፡፡ የዛህራ ገልገላ ኅበና የሙዳ በዓል የሼኽ ሁሴንን የውልደት፣ የህልፈትና የእሳቸው ተማሪዎች የመገናኛ ቀንን ለማሰብ ነው፡፡ የኢድ-አል አድሃ የሙዳ በዓል ደግሞ ነብዩ ኢብራሂም ልጁን ለመሰዋት የተዘጋጀበትን ቀን ምክንያት በማድረግ የሚከበር ነው፡፡ በመሆኑም የሙዳ ስርዓተከበራዎች በመታሰቢያ የስርዓተከበራ ምደባ ስር የሚካተቱ ናቸው፡፡

የዚህን ጥናት አቢይ ዓላማ ከግብ ለማድረስ የተሰበሰቡ መረጃዎችን ለመተንተን የክወና ንድፈሃሳብ (Performance Theory) እና ትዕምርታዊ ንድፈሃሳብ (Symbolism) ጥቅም ላይ ወለዋል፡፡

የክወና ንድፈ ሀሳብ በክወና፣ በክወና ለውጦች፣ በከዋኞችና በታዳሚዎች መካከል ያለውን ግንኙነት ለማሳየት የሚረዳ ነው (Schenchner, 2004)፡፡ የክወና ንድፈሀሳብን መሰረት በማድረግ በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነቅርስ የሚከወኑ የሙዳ ስርዓተከበራዎች፣ ስርዓተከበራዎቹ ያላቸውን የክወና ቅደምተከተል፣ በክወናው ላይ ለውጥ የሚፈጥሩ ጉዳዮች፣ የክወናው መልዕክት፣ የክወናው መዋቅር፣ ለክወናው ትዕምርት የሆኑ ጉዳዮች፣ ትዕምርቶቹ ያላቸውን ትርጓሜና የሚፈጥሩትን ተግባቦት፣ ክወናው በታዳሚውና በከዋኙ መካከል ስለሚፈጥረው ተግባቦት፣ በክወናው ወቅት በታዳሚውና በከዋኙ ላይ የሚፈጥረው የስሜት ለውጥና ለለውጡ የሚሰጥ ምላሽ በትንታኔ ለማሳየት ተሞክሯል፡፡

ትዕምርታዊ ንድፈሃሳብ ስርዓተከበራዎች ያላቸውን ትርጉም፣ ልዩ ዋጋ፣ ውክልና፣ መልዕክትና የሚፈጥሩትን ስነልቡናዊ ለውጦች የምናጠናበት እንደሆነ Turner (1969)፣ Geertz (1973) እና Bell (1977) ይገልጻሉ፡፡ ይህ ጥናት ትዕምርታዊ ንድፈሃሳብን መሰረት በማድረግ በሙዳ በዓላት ወቅት የሚከወኑ ስርዓተከበራዎች ያላቸው ትዕምርታዊ ውክልና፣ ከዋኞቹ የሚጠቀሟቸው ቁሳዊ ባህሎች ያላቸው ውክልና፣ የሚቀርቡ ክወናዎች የሚፈጥሩት የእርስበርስ ተግባቦትና የሚያሳዩት የኃይል መስተጋብር በትንታኔ ለማሳየት ጥረት ተደርጓል፡፡

## የአጠናን ዘዴ

ይህ ጥናት አይነታዊ ምርምር (Qualitative research) ነው፡፡ ለጥናቱ ጠቃሚ የሆኑ ቀዳማይና ካልዓይ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ ቀዳማይ መረጃዎች የተሰበሰቡት ከመስክ ስራ (Field work) ነው፡፡ በመስክ ስራ ወቅት መረጃዎች የሚሰበሰቡት በምልከታና በቃለመጠይቅ እንደሆነ Goldstein (1964) ይገልጻል፡፡ Kothari (2004, p. 96) ምልከታ መደበኛ (Structured) እና ኢ-መደበኛ (Unstructured) በሚሉ ሁለት አይነት ስልቶች እንደሚመደብ ይገልጻል፡፡

ይህ ጥናት አይነታዊ በመሆኑ መደበኛ ምልከታን ተግባራዊ አድርጓል፡፡ መደበኛ ምልከታ በሶስት መንገድ እንደሚካሄድ Kothari (2004) ይገልጻል፡፡ እነሱም፤ አጥኚው በመስክ ላይ የሚከወኑ ድርጊቶችን እየተገበረ ምልከታ የሚያደረግበት ተሳታፊ ምልከታ፣ አጥኚው ከዋኞቹ የሚከውኗቸውን ድርጊቶች ሳይከውን ምልከታ ብቻ የሚያደርግበት፣ እና ከዋኞቹ ድርጊቶችን በሚከውኑበት ወቅት አጥኚው በስፍራው ስለመኖሩ ፍንጭ ሳይሰጥና ከዋኞቹም ሳያውቁ በድብቅ ምልከታ የሚያደርግበት ናቸው፡፡ እነዚህ ሶስት የምልከታ መንገዶች በጥናቱ ወቅት የስርዓተከበራዎቹ የአከዋወን ሂደት፣ ድርጊትና ቅደምተከተል ላይ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ተግባራዊ ተደርገዋል፡፡

ምልከታ የምናካሂድባቸው አውዶች በተለያዩ መንገዶች ሊገኙ ይችላሉ፡፡ እነዚህን አውዶች Goldstein (1974) ተፈጥሯዊና አርቲፊሻል በሚል በሁለት ሲመድባቸው፣ ፈቃደ (1991 ዓ.ም) ደግሞ በእነዚህ ሁለት ምደባዎች ላይ ቅንብር ተፈጥሯዊ (Induced natural) የሚል አውድ በመጨመር በሶስት ይከፍላቸዋል፡፡ በዚህ ጥናት ምልከታ የተካሄደው በመካነቅርሱ በሚከበሩ የ'ኢድ-አል-አድሃ' (አረፋ) እና የ'ዛህራ ገልገላ ጎበና' የሙዳ በዓላት ወቅት በስፍራው በመገኘት በተፈጥሯዊ የምልከታ አውድ ነው፡፡

ቃለመጠይቅ መደበኛ (Structured) እና ኢ-መደበኛ (Unstructured) በሚሉ ሁለት አይነት ስልቶች እንደሚዋቀር Kothari (2004) ይገልጻል፡፡ በዚህ ጥናት ኢ-መደበኛ የቃለመጠይቅ ስልትን መሰረት በማድረግ መረጃ ተሰብስቧል፡፡ በጥናቱ ላይ የተሳተፉ መረጃ ሰጪዎች ብዛት አስራ አንድ ናቸው፡፡ በቃለመጠይቁ፤ በመካነቅርሱ የሚከወኑ የተለያዩ መንፈሳዊ ስርዓተከበራዎች ያላቸው መንፈሳዊ ትርጓሜ፣ ስርዓተከበራዎቹ ለምንና እንዴት እንደሚከወኑ፣ እና መንፈሳዊ ስርዓቶቹ ለአማኞቹ ያላቸው ማህበራዊ፣ መንፈሳዊና ስነልቡናዊ ፋይዳ በሚመለከት መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡

## የሙዳ ስርዓተከበራ፣ በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነቅርስ

የሙዳ በዓላት 'የኢድ-አል አድሃ' እና 'ዛህራ ገልገላ ጎበና' ናቸው፡፡ የኢድ-አል አድሃ በዓል በእስልምና የጊዜ አቆጣጠር ካሉት አስራ ሁለት ወራት መካከል በዱል-አል-ሒጃ ወር የሚከበር ነው፡፡ ዱል-አል-ሒጃ በሂጅራ የጊዜ ቆጠራ የመጨረሻው ወር ነው። የኢድ-አል አድሃ የበዓል የሚከበረው በዱል-አል-ሒጃ ወር በገባ በ10ኛው ቀን ነው (Gulevich, 2005)፡፡

'ዛሕራ ገልገላ ጎበና' በኦሮምኛ የሙሉ ጨረቃ ምሽት የሚል ትርጉም አለው፡፡ ይህም በዓሉ መከበር የሚጀምረው ሙሉ ጨረቃ በምትወጣበት ዕለት መሆኑን ለማመልከት ነው፡፡ የዛሕራ ገልገላ ጎበና በዓል የሚውልበት ቀን የራሱ የአቆጣጠር ስልት አለው፡፡ ይህም በሂጅራ የጊዜ ቆጠራ በ6ኛው ወር (ጁማዳ አል-አክሂራ) አጋማሽ ላይ ነው፡፡ በዓሉም በ6ኛው ወር አጋማሽ በ15ኛው ቀን ላይ ወይም ከ15ኛው ቀን አቅራቢያ ጨረቃ ሙሉ ሆና በምትወጣበት ዕለት የሚከበር ነው፡፡[2]

---

[2] - አቶ ኑማን መሃመድ፣ አናጂና ቀበሌ፣ ቃለመጠይቅ፣ መስከረም 12 ቀን 2008 ዓ.ም፡፡

በሙዳ በዓል ወቅት የሚከወኑ ስርዓተከበራዎች በዋናነት ሶስት ናቸው፡፡ እነሱም፤ በዋሬ ስፍራ፣ በከራ ጉዶ እና በቅጽር ግቢው ውስጥ እንዲሁም በአይናገኜ ገደል የሚከወኑ ናቸው፡፡ እነዚህን ስርዓተከበራዎች ያላቸውን የክወና ቅደምተከተልና ያላቸውን ትዕምርታዊ ውክልና በተናጠል ቀጥለን እንመልከት፡፡

## የዋሬ ስርዓተከበራ

"ዋሬ" የሚለው ቃል የኦሮምኛ ቃል ሲሆን፣ በመካነ ቅርሱ ሶስት ጽንሰሃሳቦችን ይገልጻል፡፡ አንደኛው፤ ስብሰባ (መሰባሰብ) ማለት ነው፡፡ ሁለተኛው፣ በስብሰባው ወቅት የሚከወኑ ስርዓተከበራዎችን ሲሆን፣ ሶስተኛው ደግሞ የመሰብሰቢያ ቦታው ነው፡፡ በመካነቅርሱ መንፈሳዊ ተጓዦች በጋራ የሚሰባሰቡበት ስፍራና ተሰባስበው የሚከውኑት ስርዓት በጥቅሉ ዋሬ ይባላል፡፡

በሙዳ በዓላት ወቅት በመካነቅርሱ የሚመጡ መንፈሳዊ ተጓዦች በአንድ ላይ በመሰባሰብ የተለያዩ ስርዓቶችን ይፈጽማሉ፡፡ በመካነቅርሱ የዋሬ ስርዓተከበራዎች የሚከወኑባቸው ስፍራዎች ሁለት ሲሆኑ፤ ዶቆ ከራ እና ዶቆ ድንኩሬ በሚሉ ስያሜዎች ይጠራሉ፡፡ በእነዚህ ስፍራዎች የተገነቡ የደረጃ መቀመጫዎች አሉ፡፡ የደረጃ መቀመጫዎቹም በ18ኛው መቶ ክፍለዘመን መጨረሻ ላይ በሼኽ መሃመድና በሼኽ አባስ እንደተገነቡ የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነ ቅርስ ባህልና ቱሪዝም ጽህፈት ቤት የቀረበ ሪፖርት (2002 ዓ.ም) ይገልጻል፡፡



ፎቶ 1- የመካነቅርሱ ዋና የመግቢያ በር እና ዶቆ ከራ የዋሬ ስርዓተከበራ የመከወኛ ስፍራ፡፡ (ፎቶ በአጥኚው)

በእነዚህ የዋሬ ስፍራዎች የሚከወኑ ስርዓተከበራዎች የሚከወነው ቀንና ሌሊት (ሀያ አራት ሰዓት) ሲሆን ክወናቸውም በተመሳሳይ ቅደምተከተል ነው፡፡ በሁለቱም የሙዳ በዓላት ወቅት ምሽት ላይ የሚከወነው የዋሬ

ስርዓተከበራ የሚጀምረው ቅዱስ ቁርዓን በመቅራት ነው፡፡ ቁርዓን የመቅራት ስርዓት ሲጠናቀቅ የ"ሰለዋት" ስርዓት ይጀመራል፡፡ በስርዓቱም አላህ፣ ነብዩ መሃመድ፣ ሼኽ ሁሴንና ሼኽ ሶፍ ዑመር[3] ይወደሳሉ፡፡

በሁለቱ ስፍራዎች የሚከወኑ ስርዓተከበራዎችን የሚመሩ የፕሮግራም አስተባባሪዎችና ወንበራ አሉ፡፡ ወንበራ የሚል የማዕረግ ስም የሚሰጣቸው የዋሬ ስርዓተከበራ ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ ድረስ ዋሬው መሃል በተዘጋጀላቸው ልዩ ቦታ ቆመው ወይም ቁጭ ብለው ፕሮግራሙን በበላይነት የሚመሩ ናቸው፡፡ የዋሬ ስርዓተከበራዎች የባሮ መንፈሳዊ ሙዚቃ፣ የሂክማ፣ የአርጆማ፣ ስለት የማስገባት፣ የጪንጫ፣ የምረቃ፣ የእርግማን፣ የምህላና የሰርመዴ መንፈሳዊ ሙዚቃ ናቸው፡፡ እነዚህን ስርዓተከበራዎች ያላቸውን የክወና ቅደምተከተልና ያላቸውን ትዕምርታዊ ውክልና በተናጠል ቀጥለን እንመልከት፡፡

## የባሮ መንፈሳዊ ሙዚቃ ክወና

የባሮ መንፈሳዊ ሙዚቃ በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነቅርስ ከሚከወኑ መንፈሳዊ ሙዚቃዎች መካከል አንዱ ነው፡፡ "ባሮ የሚለው ቃል የአረብኛ ቃል ከሆነው ‹ባሕር› የተገኘ ሲሆን፣ ‘ባሕር’ ሼኽ ሁሴንን ለማወደስ የሚያገለግል ቃል ነው" (Jeylan, 2005, p. 34)፡፡ ተከታዮቻቸው ሼኽ ሁሴንን ሲያወድሱ ‘ባሕረዎ’ ይሏቸዋል፡፡ ‘ባሕረዎ’ ማለት የአረብኛውን ባሕር የሚለውን ቃል ‘ኦሮምኛዊ’ (Oromofication) በማድረግ ‘ባሕር የሆኑ’ ለማለት ነው፡፡ ቃሉም ሼኽ ሁሴን ባሕር መሆናቸውን ይገልጻል፡፡ ባህር የሚለው ትዕምርት ሆደ ሰፊ፣ ቻይ፣ ታጋሽና ትዕግስተኛ የሚሉትን እሳቤዎች ለመግለጽ የሚጠቀሙበት ነው፡፡

የባሮ መንፈሳዊ ሙዚቃ ሼኽ ሁሴንን ለማወደስ በግጥም ቅርጽ የሚቀርብ ነው፡፡ በመንፈሳዊ ሙዚቃውም የሼኽ ሁሴንን ተዓምራት፣ ፈጥኖ ደራሽነት፣ ታጋሽነትና ሩሕሩሕነት ይገለጽበታል፡፡[4] በባሮ ከሼኽ ሁሴን በተጨማሪ ፈጣሪን፣ ነብዩ መሃመድን፣ ሼኽ ሶፍ ዑመርን እና ሼኽ ሁሴንን ለመጎብኘት ከባግዳድ ወደ ስፍራው እንደመጡ

[3] - ሼኽ ሶፍ ዑመር የሼኽ ሁሴን ተማሪ እንደሆኑ ይነገራል፡፡ በባሌ ዞን የሚገኘው የሶፍ ዑመር ዋሻ፣ እሳቸው የመሰረቱት መንፈሳዊ መካነቅርስም በስማቸው ይጠራል፡፡

[4] - ሼኽ ኢብራሂም ሲራጅ፣ አናጂና ቀበሌ፣ ቃለመጠይቅ፣ ሚያዝያ 7፣ ቀን 2008 ዓ.ም፡፡

የሚነገርላቸውና የቃድሪያ ስርዓት መስራች የሆኑት ሼኽ አብዱልቃዲር ጀይላኒ ናቸው፡፡ የቃድሪያ ስርዓት በሱፊዝም ታሪክ የመጀመሪያው መደበኛ የሱፊዝም ስርዓት ነው (Renard, 2009)፡፡

የባሮ መንፈሳዊ ሙዚቃ ሼኽ ሁሴን ለሰዎች (ለግለሰቦች) የዋሉትን ውለታ፣ በክፉ ቀን እንዴት ፈጥነው እንደደረሱላቸው ይገልጹበታል፡፡ ከእነዚህ መንፈሳዊ ጉዳዮች በተጨማሪ በስፍራው ተከስተዋል ተብለው የሚታመኑ ሚቶችን፣ ታሪካዊ ሁነቶችን፣ የሼኽ ሁሴን ተከታዮች መከወን ስለሚገባቸው ስነምግባራዊ ጉዳዮች፣ ወቅታዊ የፖለቲካ ጉዳዮች እንዲሁም ወደፊት የሚፈጸሙ ሁነቶችን (ትንቢቶችን) በባሮ አማካኝነት ይገልጻሉ፡፡

የባሮ መንፈሳዊ ሙዚቃ በዋሬ ስርዓት ወቅት እንዲሁም በቤት ውስጥ ሰዎች ሰብሰብ ብለው በሚከውኑት የሀድራ ስርዓት ላይ የሚቀርብ ነው፡፡ የባሮ መንፈሳዊ ሙዚቃ ግጥም በአብዛኛው በኦሮምኛ ቋንቋ የሚቀርብ ነው፡፡ የባሮ መንፈሳዊ ሙዚቃ በኦሮምኛ ሲቀርብ በግጥሞቹ ውስጥ አልፎአልፎ የአማርኛ፣ የአረብኛ፣ የእንግሊዝኛ፣ የሱማልኛ እንዲሁም አንድን ቃል ከአንድ ቋንቋ (ከአረብኛ ወይም ከአማርኛ) በመውሰድ ኦሮምኛዊ ሆነው የተፈጠሩ ቃላትና ሀረጋት ይደባለቅበታል፡፡

በዋሬ ስርዓት ላይ ባሮ የሚቀርበው የተለያዩ ስርዓቶች በሚከወኑበት ወቅት መሀል መሀል ላይ ነው፡፡ የባሮ መንፈሳዊ ሙዚቃን የሚያቀርቡ ባለሙያዎች 'ኡሌ' በሚል የማዕረግ ስም ይጠራሉ፡፡ አንዱ ኡሌ ተነስቶ ባሮ ይላል፡፡ አንዱ ኡሌ ባሮ እያለ ሲደክመው ሌላው ኡሌ ይቀበለዋል፡፡ ኡሌዎቹ አንዱ ከሌላው እየተቀበለ በየተራ ባሮ ይላሉ፡፡ ኡሌዎች እየተቀባበሉ ባሮ ማለት ከጀመሩ ስሜት ውስጥ እየገቡና ይበልጥ እየተመሰጡ ይሄዳሉ፡፡ ኡሌዎች ለበርካታ ደቂቃዎች ያለማቋረጥ የባሮ መንፈሳዊ ሙዚቃ ሲያቀርቡ በመስክ ቆይታዬ ወቅት አይቻለሁ፡፡

ኡሌዎች የባሮ መንፈሳዊ ሙዚቃ ሲያቀርቡ በዋሬ ላይ በተሰበሰበው ሕዝብ መሃል በመቆም፣ ወይም ከፍ ያለ ቦታ ላይ በመውጣት ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ነው፡፡ ባሮ ሲሉም በቀኝ እጃቸው የባላ ቅርጽ ያለው ረጅም በትር ('ደንቄ') በመያዝ፣ በትሩንም ወደፊት፣ ወደ ላይ፣ ወደ ጎን በቀስታ በማወዛወዝ፣ ትከሻቸው ላይ በማድረግ እንዲሁም የግራ እጅ አመልካች ጣታቸውን በግራ የጆሯቸው ቀዳዳ ውስጥ በመክተት ይከውናሉ፡፡ የተሰበሰበው ሕዝብ የግጥሙን አዝማች ከኡሌው ጋር በአንድ ላይ በመድገምና በማዜም፣ በጥሞና በማዳመጥ፣ በማልቀስ፣ የጭብጨባ ድጋፍና የተለያዩ ሽልማቶችን በመስጠት የባሮ ክወና ተሳታፊ ይሆናል፡፡

### የሂክማ ስርዓተከበራ

በዋሬ ላይ ከሚከወኑ ስርዓተከበራዎች መካከል አንዱ ‘ሂክማ’ ነው፡፡ ‘ሂክማ’ የአረብኛ ቃል ሲሆን፣ ጥበብ፣ ተዓምር፣ ምስጋና የሚሉ ትርጉሞች አሉት፡፡ በመካነ ቅርሱ የሂክማ ስርዓተከበራ ተዓምራትን የመመስከርና ምስጋና የማቅረብ ስርዓት ነው፡፡ ይህ ስርዓት መንፈሳዊ ተጓዦቹ ከዚህ በፊት የነበረባቸውን ችግር ለሼኽ ሁሴን በመንገር፣ ከነበረባቸው ችግር መፈወሳቸውን፣ በስፍራው መጥተው በስፍራው የሚገኘውን ቅዱስ አፈር (‘ጀዋራ’) ከተቀቡና በስፍራው የሚገኝን የዘምዘም ጸበል ከጠጡ በኋላ ከነበረባቸው የጤና ችግር መፈወሳቸውን፣ በስፍራው ደርሰው ከተመለሱ በኋላ ከነበረባቸው የገንዘብ፣ የሰላም፣ የጤንነት፣ የስኬት የመሳሰሉት ችግሮች መውጣታቸውን ተራ በተራ በተሰበሰበው ሕዝብ ፊት በመውጣት የሚገልጹበትና ምስጋና የሚያቀርቡበት ነው፡፡[5]

በሂክማ ስርዓተከበራ ወቅት ምስጋና አቅራቢዎች ለራሳቸው በተጨማሪም በቤተሰባቸው፣ በጓደኞቻቸውና በጎረቤቶቻቸው የደረሰላቸውን ይናገራሉ፡፡ ምስጋናቸውን የሚያቀርቡ ግለሰቦች ከዚህ በፊት ደርሶባቸው የነበረው ችግር ምን እንደነበርና ከነበረባቸው ችግር ተላቀው አሁን በምን ደረጃ ላይ እንደደረሱ በግልጽ የመናገርም ግዴታ አለባቸው፡፡ እነዚህን ነገሮች በግልጽ መናገር ያለባቸው አንድም የሼኽ ሁሴንን ተዓምራትና ፈጥኖ ደራሽነት ለተሰበሰበው ሕዝብ ለማሳወቅ፣ አንድም የሚደብቁት ወይም መናገር ሲገባቸው ያልተናገሯቸው ቢኖሩ የሼኽ ሁሴንን ውለታ ማሳነስ ተደርጎ ስለሚታመን ነው፡፡

ግለሰቡ ላይ የደረሰው አይነት ችግር በስፍራው በተሰበሰቡ መንፈሳዊ ተጓዦችና በቤተሰባቸው ላይ እንዳይከሰት ሕዝቡ ይመረቃል፡፡ ግለሰቡም ሆነ ሕዝቡ ሲመረቅ በስፍራው የተሰበሰቡ ሰዎች ሁሉ ‘አሜን’ በማለት ምርቃቱን ይቀበላሉ፡፡ ግለሰቡን ሕዝቡ በቱፍታ እንዲመርቀው የፕሮግራም አስተባባሪው ይጠይቃል፡፡ ቱፍታ፣ ምራቅን ቱፍ-ቱፍ በማድረግ የሚከወን የምረቃ አይነት ነው፡፡ ሕዝቡም ግለሰቡን ሲመርቅ፣ ግለሰቡ አሜን በማለት ይቀበላል፡፡

በከዋኞች አማካኝነት በቃል የሚተላለፉ ታሪኮች በአድማጮች ዘንድ በአግባቡ እንዲደርሱና የተፈለገውን መልዕክት እንዲያስተላልፉ የሚጠቀሟቸው የተለየዩ ስልቶች አሉ፡፡ እነዚህን ስልቶች የምናጠናባቸው መንገዶች የተለያዩ ናቸው፡፡ ከእነዚህ መንገዶች መካከል

---

[5] - አቶ ኑማን ሼኽ መሐሙድ፣ አናጂና ቀበሌ፣ ቃለመጠይቅ፣ መጋቢት 26፣ ቀን 2008 ዓ.ም፡፡

Jafferson (1973) የፈጠረው አውዳዊ ተግባቦትን መሰረት ያደረገ ታሪክ (Contexted occurrence of stories in conversation) አንዱ መንገድ እንደሆነ ይገልጻል፡፡ የዚህ መንገድ ዋናው ትኩረት የአድማጭን ስሜት በመቆጣጠር የታሪኩ ተጋሪ የሚሆንበትን ስልት መተንነተን ነው፡፡ በትረካው ወቅትም አድማጩ በትረካው የሚሰማው ታሪክ የራሱ ታሪክ እንደሆነ እንዲያስብ፣ የራሱን ቀደምት የሕይወት ተመክሮውን በማስታወስ ከታሪኩ ጋር ማገናኘት፣ ታሪኩን በሙሉ ስሜትና የእኔ ገጠመኝ ነው በሚል ስሜት በትክክል አዳምጦ ለሌሎች እንዲያስተላልፍ ማድረግ ነው (Jafferson, 1973)፡፡

በዚህ መንገድ አድማጩ ለሚቀርበው ታሪክ ረዳት-ከዋኝ (Co-producer) ሚና አለው፡፡ አድማጩ ይህንን ሚናውን የሚወጣው ታሪኩን በሚያዳምጥበት ወቅት የተለያዩ የሰውነት እንቅስቃሴዎችን በማድረግ ነው፡፡ የአድማጩ የሰውነት እንቅስቃሴዎችም ጭንቅላትን መነቅነቅ፣ አንገትን ወደ ላይ መሳብ፣ የሰውነት አቀጣጫን መቀየር፣ ዐይን ዐይንን ማየት፣ ጥያቄ ማቅረብ (ከዛ እንዴት ሆነ፣ ቀጥሎስ፣ እሺ አይነት አገላለጽ) የመሳሰሉት ናቸው፡፡[6]

በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነቅርስ በተለያዩ ግለሰቦች ሂክማ ሲቀርብ ታዳሚው ሂክማውን ከልብ እንዲያዳምጥ የፕሮግራም መሪዎች የተለያዩ ዘዴዎችን ይጠቀማሉ፡፡ ሂክማውን ለመናገር ሕዝብ ፊት የሚቆም ግለሰብ ሂክማውን መናገር ከመጀመሩ በፊት፣ የፕሮግራም መሪው "የሼኽ ሁሴንን ተዓምር ሁላችሁም ስሙ"፤ "ለሼኽ ሁሴን ሂክማ ምስክር ናችሁ"፤ "አድምጡ-አድምጡ!"፣ "ይኸው-ይኸው!" የሚሉ አገላለጾችን በመጠቀም አድማጩ ለሂክማው ትኩረት እንዲሰጥና በጥሞና እንዲያዳምጥ ያደርጋሉ፡፡ ሂክማውን የሚናገረው ግለሰብ ታሪኩን ሲናገር መሃል መሃል ላይ የፕሮግራም መሪው በድምጽ ማጉያ ለሁሉም ሕዝብ እንዲሰማ በማድረግ ይናገራል፡፡

## የአርጆማ ስርዓተከበራ

"አርጆማ" የኦሮምኛ ቃል ሲሆን፣ ስጦታ ወይም እርዳታ የሚል ትርጉም አለው፡፡ ይህ ቃል በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነቅርስ "ኒያ" ከሚለው ቃል ጋር በአቻዊነት ያገለግላል፡፡ "ኒያ" የአረብኛ ቃል ሲሆን፣ ካሉት የተለያዩ ትርጉሞች መካከል አንዱ ስጦታ መስጠት ነው፡፡ በስፍራውም

6 - Jafferson (1973) እነዚህን የሰውነት እንቅስቃሴዎች በምሳሌ ቢያመጣም፣ የሰውነት እንቅስቃሴዎች አካባቢያዊ፣ ባህላዊና ኃይማኖታዊ ትርጓሜያቸው በየአካባቢው እንደሚለያዩ ከግምት ማስገባት ይኖርብናል፡፡

እነዚህን ሁለት ቃላት በመቀያየር መጠቀም የተለመደ ነው፡፡ በመካነቅርሱ ስጦታ የመስጠት ስርዓተከበራ አርጆማ በሚል ይታወቃል፡፡ የአርጆማ ስርዓተከበራም በዋሬ ስፍራ የተሰበሰበው መንፈሳዊ ተጓዥ ለተለያዩ አካላት ስጦታ የሚሰጥበት ነው፡፡

አንድ ግለሰብ በሰማው ችግር ሀዘን ሲሰማው እራሱ የለበሰውን ጃኬት፣ ሱሪ፣ ሸሚዝ፣ ሹራብ ወይም ፎጣ ሕዝብ ፊት አውልቆ ሊሰጥ ይችላል፡፡ ግለሰቡ በስሜት ሆኖ የለበሰውን ልብስ አውልቆ ሲሰጥ "ሌላ ተቀያሪ ልብስ አለኝ? ይህ አዲስ ነው፣ ይህን ብሰጥ ይሻላል ወይም ይህ ልብስ ለግለሰቡ ይሆነዋል?" የሚሉ ሀሳቦችና ጥያቄዎች በአዕምሮው አይመጡም፡፡ በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነቅርስ የዋሬ ስርዓተከበራ ወቅት የለበሱትን ልብስ አውልቀው ችግሩን ለተናገረ ግለሰብ ስጦታ ሰጥተው እርቃናቸውን ወደ ተቀመጡበት ስፍራቸው የሚመለሱ ግለሰቦችን በመስክ ቆይታዬ ወቅት ተመልክቻለሁ፡፡

ለእነዚህ ግለሰቦች ደግሞ ሳያስቡት ሌላ ግለሰብ የለበሰውን ልብስ አውልቆ ይሰጣቸዋል፡፡ ልብሱን አውልቆ ለሰጠውም ግለሰብ ደግሞ ሌላ ግለሰብ የራሱን አውልቆ ይሰጣል፡፡ ይህ አይነት የስጦታ አሰጣጥ ሂደት መንፈሳዊ ተጓዦቹ ያላቸውን የእርስበርስ ፍቅር፣ ተደጋጋፊነት፣ ተስፋነትና አለኝታነት የሚያሳይ ነው፡፡

ግለሰቦች ስጦታ ሲሰጡ፣ በምትኩ ምርቃት፣ ፈውስ ወይም ሌላ ችሮታ ፈልገው ሊሆን ይችላል፡፡ በተለያዩ ምክንያቶች በመካነቅርሱ ለሚኖሩ ግለሰቦች የሚሰጥ ስጦት፣ ለሰጪው አካል የአጸፋ ስጦታ ያስገኝለታል፡፡ የአጸፋ ስጦታውም ምርቃት ወይም አክብሮት ሊሆን ይችላል፡፡ ምረቃውን የተቀበለ አካልም የሚፈልገው ነገር እንዲሳካለት፣ ጤና እንዲሰጠው ወይም በአካባቢው የዝናብ፣ የድርቅ፣ የበሽታ ችግር ካለም ከችግር እንዲወጡ ይመርቃቸዋል፡፡ በመካነ ቅርሱ ማንኛውም ግለሰብ የሚመርቀው ምርቃት ይደርሳል ተብሎ ይታመናል፡፡ በመሆኑም የአርጆማ ስርዓተከበራ የመለዋወጥ ውክልና (Symbolic exchange) ነው፡፡

## ስለት የማስገባት ስርዓተከበራ

በሼኽ ሁሴን የሚያምኑ ግለሰቦች ካለባቸው ችግር ለመፈወስ ወይም የሚፈልጉትን ነገር ለማግኘት ይሳላሉ፡፡ ግለሰቦቹ ስለት የሚሳሉት በመካነቅርሱ በአካል በመገኘት ወይም በሚኖሩበት ስፍራ ሆነው ነው፡፡ ግለሰቦች ካለባቸው የጤና፣ የኢኮኖሚ ወይም ሌሎች ችግሮች ለመዳን እንዲሁም በሕይወታቸው ማግኘት የሚፈልጉትንና የሚመኙትን ነገር ለማግኘት ሲፈልጉ፣ ሼኽ ሁሴን ከእነዚህ ችግሮች ከፈወሷቸው አቅማቸው የፈቀደውን ነገር ይዘው እንደሚመጡ ወይም በሰው እንደሚልኩ ስለት ይገባሉ፡፡

ግለሰቦቹ ከነበረባቸው ችግር ሲፈወሱ ወይም የሚፈልጉትን ነገር ሲያገኙ ቃል በገቡት መሰረት ስለታቸውን ይዘው ወደ ስፍራው ይመጣሉ ወይም በሰው ይልካሉ፡፡ ግለሰቦች ስለት አስገባለሁ ብለው የሚሳሉት የተለያዩ ነገሮችን ሊሆን ይችላል፡፡ ከእነዚህ መካከል የእርድ ከብት፣ ገንዘብ፣ ልብስ፣ ቡና፣ እህል፣ ጫት፣ እጣን፣ ሰንደል የመሳሰሉት የተለመዱ ናቸው፡፡

በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነቅርስ ሁለት አይነት ስለት የማስገቢያ መንገድ አለ፡፡[7] አንደኛው፣ ስለት የሚያስገባው ግለሰብ በመካነቅርሱ በቋሚነት የሚያርፍበት ቤት ያለው ሲሆን፣ ሁለተኛው፣ ደግሞ በመካነቅርሱ ቋሚ ማረፊያ ቤት የሌለው ነው፡፡ ስለት የሚያስገባው ግለሰብ በቋሚ የሚያርፍበት ቤት ካለው፣ ስለቱን ከማስገባቱ በፊት፣ ስለተሳለበት ነገር ለቤቱ ባለቤት (አባወራ) ይናገራል፡፡ ስለቱንም ይዞ መምጣቱን ይገልጻል፡፡ ግለሰቡ ይዞት የመጣውን ስለት ሲያስገባም የቤቱ ባለቤት አብሮት በዋሬው ስፍራ ላይ ይገኛል፡፡

ግለሰቡ ይዞት የመጣውን ስለት ለቤቱ ባለቤት ያስረክባል፡፡ ቋሚ ማረፊያ ያለውና በዋሬው ስፍራ ከቤቱ ባለቤት ጋር በመሆን ስለቱን የተናገረ ሰው አመጣለሁ ብሎ ቃል የገባውን ነገር ይዞ ሲመጣ ለቤቱ ባለቤት ያስረክባል፡፡ በግለሰቡ የመጣውን ስለትም ከእርድ ከብት ውጪ ገንዘብ፣ አልባሳት ወይም ሌላ ነገር ከሆነ የቤቱ ባለቤት ለግሉ በመውሰድ ይጠቀምበታል፡፡ ነገር ግን ግለሰቡ ለስለት ይዞ የመጣው የእርድ ከብት ከሆነ ታርዶ የአካባቢው ሰው በጋራ ይመገባል፡፡ የቤቱ ባለቤት ለስለት የመጣውን የእርድ ከብት መሸጥም ሆነ ማርባት አይችልም፡፡

በመካነ ቅርሱ ቋሚ ማረፊያ ቤት የሌለው ግለሰብ ደግሞ የገባውን ስለት ሕዝቡ ፊት እራሱ ይናገራል፡፡ ሕዝቡም ስለቱ ስለተሰማለት ይመርቀዋል፡፡ ይዞት የመጣውን ስለት የፕሮግራሙ አስተባባሪዎች ተቀብለው በዋሬው ስፍራ ለሚገኙ ችግረኞች እዛው ያከፋፍላሉ፡፡ ግለሰቡ ለስለት ይዞት የመጣው የእርድ ከብት ከሆነም ታርዶ ስጋው ለሕዝቡ ይከፋፈላል፡፡

### የጪንጫ ስርዓተከበራ

ጪንጫ፤ ሽታ ከሚለው ቃል ጋር ተቀራራቢ ትርጉም አለው፡፡ የጪንጫ ስርዓተከበራ ለእርድ ከቀረበው ከብት ሽታውን መስዋዕት

---

[7] - ሼኽ በክሪ ሼኽ መሃመድና አቶ መሃመድ ሼኽ መሃሙድ፣ አናጂና ቀበሌ፣ ቃለመጠይቅ፣ መስከረም 12 ቀን 2008 ዓ.ም፡፡

የማድረግ ክወና ነው፡፡[8] ግለሰቦች የከብት እርድ ይሳላሉ፡፡ ስለታቸው ሲደርስላቸው በስፍራው የከብት እርድ ያካሂዳሉ፡፡ ከስለት በተጨማሪም ግለሰቦች በፍላጎታቸው የእርድ ከብት ይዘው በመምጣት በስፍራው ያለውን ሕዝብ ያበላሉ፡፡ ለስለትም ይሁን ለስጦታ በሚታረድ ከብት ላይ የጪንጫ ስርዓተከበራ ይፈጸማል፡፡ ጪንጫ በስፍራው ከታረደው ግመል፣ በግ፣ ፍየል፣ በሬ ወይም ላም የተወሰኑት አካላትን በእሳት የማቃጠል ስርዓተከበራ ነው፡፡ ከእርድ ከብቱ አካላት መካከል ጭንቅላቱንና አራቱ ኮቴዎቹን በግራር እንጨት በተቀጣጠለ እሳት ያቃጥሉታል፡፡



ፎቶ፣2፣ የጪንጫ ስርዓት በዶቆ ከራ ስፍራ ሲከወን የሚያሳይ፡፡ (ፎቶ በአጥኚው)፡፡

በስፍራው የተገኘ ሰው የከብቱን ስጋ ይበላል፡፡ በስፍራው ከሰው ልጅ በተጨማሪ ረቂቅ መናፍስት አሉ ተብሎ ይታመናል፡፡ ረቂቅ መናፍስት የሚፈልጉት ስጋውን ሳይሆን ሽታውን ነው፡፡ በመሆኑም ጪንጫ የሚደረገው በስፍራው ለሚገኙ ረቂቅ መናፍስት ምግብ እንዲሆናቸው ነው፡፡ ጪንጫ የከራና የቤት በሚል በሁለት ይመደባል፡፡ ግለሰቡ ለስለት ይዞ የመጣውን የእርድ ከብት በመካነቅርሱ ዋና የመግቢያ በር አካባቢ በሚገኘውና ከራ ተብሎ በሚጠራው ስፍራ እንዲታረድ ከፈለገ፣ ቀደም ሲል ከራ ላይ አበላለሁ ብሎ ቃል ከገባ፣ ቋሚ የማረፊያ ቤት ከሌለው

[8] - አቶ ኑማን ሼኽ መሐሙድ፣ አናጂና ቀበሌ፣ ቃለመጠይቅ፣መጋቢት 26፣ ቀን 2008 ዓ.ም፡፡

ወይም ለስጦታ በሚል ይዞ ከመጣ በከራ ስፍራው ላይ እንዲታረድ ይደረጋል። ከብቱም ከታረደ በኋላ የሚከወን የጪንጫ ስርዓት የከራ ጪንጫ ሲባል፣ መኖሪያ ቤት አካባቢ የሚከወነው ደግሞ የቤት ጪንጫ ይባላል።

## የምርቃት ስርዓተከበራ

ለመካነቅርሱና ለአካባቢው አስተዋጽኦ ላደረጉ አካላት እንዲሁም የተለያዩ ግላዊ ጉዳዮችቻቸውን ለተናገሩ ግለሰቦች ምርቃት ይሰጣቸዋል። በዋሬ ስርዓተከበራ ወቅት የሚቀርቡ ምርቃቶች ከሚመረቁ አካላት አንጻር የግለሰቦች፣ የመንግስት፣ የተቋማት፣ የማህበረሰብ፣ የሀገር፣ የእንስሳትና የእጸዋት በሚሉ ሰባት ምደባዎች መክፈል እንደሚቻል በመስክ የተገኙ መረጃዎች ያሳያሉ።

እንደሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁሉ በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነቅርስ ለመንፈሳዊ ጉዞ የሚመጣው አብዛኛው ሕዝብ ሕይወቱ የተመሰረተው በእርሻና በከብት እርባታ ነው። በመሆኑም የእንስሳትና የሰብል ደህንነት ለሕዝቡ እጅግ አሳሳቢ ጉዳይ ነው። በመካነቅርሱም እንስሳት ጤነኛ እንዲሆኑ፣ ምርታማ እንዲሆኑና እንዲረቡ ይመረቃሉ። ሰብሉም ምርታማ እንዲሆን፣ በዝናብ እጥረት እንዳይደርቅ፣ በቁር እንዳይመታና በሰብል በሽታ እንዳይጠቃ ይመረቃል።

ሕዝቡም በሚያመርተው ሰብልና በሚያረባው እንስሳ የተሻለ ውጤት እንዲያገኝና ሕይወቱ እንዲሻሻል ይመረቃል። በመካነቅርሱ የተለያዩ አካላት ምርቃት ከተቀበሉ በኋላ በስፍራው የተገኘው ሕዝብ ጤና እንዲያገኝ፣ በሕይወቱ ደስተኛ እንዲሆን፣ የለመኑት ነገር ፈጥኖ እንዲደርስ፣ ከክፉ ችግር፣ ከምቀኛና ከሽረኛ እንዲጠበቁ ይመረቃሉ።

በስፍራው የሚመረቅ አካል ምረቃውን ሲቀበል ሕዝቡም ምርቃቱን በጋራ "አሜን" በማለት ይቀበላል። ምርቃቱ የሚጠናቀቀው እርስበርስ ሰላምታ በመሰጣጠትና እርስበርስ በመዘያየር ነው። ሰላምታ አሰጣጡና አዘያየሩ አጠገብ ከተቀመጠ ሰው ጋር እጅ ለእጅ ወይም ጉንጭ ለጉንጭ በመሳሳም ነው። ይህ የመሳሳም ሂደት የምረቃ ስርዓቱ መጠናቀቁን ከመግለጽ በተጨማሪ ወደ ሌላ ክወና መሸጋገርን የሚያሳይ የክወና ቅየሳ (Performance turn) ድርጊት ነው።

## የእርግማን ስርዓተከበራ

በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነቅርስ ከሚከወኑ ስርዓተከበራዎች መካከል አንዱ እርግማን ነው። በስፍራው እርግማን ማካሄድ እጅግ አደገኛ እንደሆነ ይታመናል። ምክንያቱም በስፍራው የተገኘ ግለሰብ በተናጠልም ሆነ፣ ሕዝብ በጋራ የተራገመው ነገር በፍጥነት ይደርሳል ተብሎ ይታመናል።

በመሆኑም በስፍራው እርግማን ማካሄድ የተለመደ አይደለም፡፡ በስፍራው እርግማን የተለመደ ባይሆንም አልፎአልፎ ይከወናል፡፡ እርግማን ጥፋት አጥፍተዋል በተባሉ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች ላይ ነው፡፡

በአሁኑ ወቅት በመካነቅርሱ በተደጋጋሚ የሚረገመው የሰለፊያ አስተምህሮን የሚከተለው የእስልምና ኃይማኖት ቡድን ነው፡፡ የሰለፊያ አስተምህሮን የሚከተሉ ኃይማኖታዊ ቡድኖች የሼኽ ሁሴንን አስተምህሮ አይቀበሉም፤ የሼኽ ሁሴን ከራማን አይቀበሉም፤ ወደ ሼኽ ሁሴን መካነቅርስ ለአምልኮ መሄድ አይገባም፤ ሼኽ ሁሴንን በተለየ መውደድ የፈጣሪን አንድ አምላክነት ላይ ሽርክ (ተጋሪ) መፍጠር ነው፤ የሼኽ ሁሴንን የቀብር ስፍራ መዘየር (መጎብኘት) አይገባም፤ ብለው የሚያምኑ ናቸው፡፡

ለቡድኖች ብቻ ተግባራዊ የሚደረጉ አራት የእርግማን ክወናዎች አሉ፡፡ እነሱም፤ አንደኛ፤ ድንጋይ ከመሬት አንስቶ እርስበርስ ማጋጨት ነው፡፡ በስፍራው የተገኘ ሕዝብ ከመሬት በቀኝና በግራ እጆቹ ሁለት አነስተኛ መጠን ያላቸው ድንጋዮች (ጠጠሮች) እንዲያነሱ ይደረጋል፡፡ በእጆቻቸው ያነሷቸውን ድንጋዮች እርስበርስ ለማጋጨት ይዘጋጃሉ፡፡ የፕሮግራም መሪውም "ምታ!" የሚል ትዕዛዝ ያስተላልፋል፡፡ ሕዝቡ የያዘውን ድንጋይ እርስበርስ ያጋጫል፡፡ ሕዝቡም በፕሮግራሙ መሪ ትዕዛዝ የያዘውን ድንጋይ ሶስት ጊዜ ያጋጫል፡፡

ድንጋይ የማጋጨት ክወናዊ ትዕምርት "ይህን ያደረገ አካል እንደዚህ ይጋጭ፣ ጭንቅላቱ እንደዚህ ይፍረስ" የሚል ትርጓሜ አለው፡፡ ሶስት ጊዜ መሆኑ እርግማኑ ሙሉና ትክክል መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ በእጃቸው የያዙትን ድንጋይ ካጋጩ በኋላ ይረግማሉ፡፡ እርግማኑን የሚናገረው የፕሮግራሙ መሪ ሲሆን፣ እሱ ያለውን ሕዝቡ በአንድ ላይ ይደግማል፡፡

ሁለተኛ፤ የእጅ ባትሪ ወደ ሰማይ ማብራት ነው፡፡ በስፍራው የተገኘና የእጅ ባትሪ የያዘ ሰው የእጅ ባትሪውን ወደ ሰማይ አቅጣጫ ያደርጋል፡፡ የፕሮግራም መሪው "አብራ!" የሚል ትዕዛዝ ሲሰጥ በስፍራው የተገኘና የእጅ ባትሪ የያዘ ሰው ሁሉ የባትሪውን ብርሃን ወደ ሰማይ አቅጣጫ ያበራል፡፡ የፕሮግራም መሪው ያበሩትን የእጅ ባትሪ "አዙር!" የሚል ትዕዛዝ ሲሰጥ ሁሉም በእጅ የያዘውን ባትሪ ሰማይ ላይ እንዳበራ፤ በክብ ቅርጽ ያሽከረክረዋል፡፡

የእጅ ባትሪን በማብራት "ዐይናቸው ላይ እንዲህ ይብራ፣ ብርሃኑም ዐይናቸውን ያጥፋው፣ እንዲህ በእሳት ይቃጠሉ" የሚሉ ትርጓሜዎች

አሉት፡፡[9] ብርሃኑን ወደ ሰማይ አቅጣጫ ማድረግ ደግሞ "ፈጣሪ ሆይ፣ ይህንን በደል ፈጽመዋልና በብርሃን ፍጥነት እርምጃ ውሰድባቸው" የሚል ትርጉም አለው፡፡[10] ባትሪ ሰማይ ላይ ማሽከርከር "ጠላት ዞሮ ዞሮ ውጤት አልባ ይሁን! ጠላት እንዲህ ይዙርበት! አሸናፊነቱ የእኛ ይሁን!" የሚሉ ትርጓሜዎች አሉት፡፡[11] እርግማኑን የሚናገረው የፕሮግራሙ መሪ ሲሆን፣ እሱ ያለውን ሕዝቡ በአንድ ላይ ይደግማል፡፡

ሶስተኛ፤ የእጅን መዳፎች እርስበርስ በኃይል ማማታት ነው፡፡ በስፍራው የተሰበሰበ ሰው ሁለት እጁን ወደ ሰማይ አቅጣጫ ይዘረጋል፡፡ የፕሮግራም መሪው "ፈትግ" ሲል፣ ሕዝቡ የእጆቹን መዳፎች እርስበርስ በፍጥነት ያፋትጋል፡፡ ከዚህ በኋላ የፕሮግራም መሪው "ምታ" የሚል ትዕዛዝ ያስተላልፋል፡፡ ሕዝቡም የእጆቹን መዳፎች እርስበርስ በኃይል ያማታል፡፡ የእጅ ምቱም ለሶስት፣ ለሰባት ወይም ለአስር ጊዜ በመቁጠር ይደጋገማል፡፡ መዳፎችን እርስበርስ በኃይል የማጋጨት ድርጊትና ግጭቱ የሚፈጥረው የጭብጨባ ድምጽ የሁሉም ሰው እኩል እንዲሆን ቁጥጥር ይደረጋል፡፡ ሁሉም ሰው እኩል የማያጨበጭብ ከሆነ የፕሮግራም መሪው እርግማኑ ድጋሚ እንዲከወን ያዛል፡፡

ሕዝቡ የእጆቹን መዳፎች እርስበርስ በፍጥነት የማፋተጉ ድርጊት በመዳፍ ውስጥ የገባውን ቡድን መጨፍለቅን፣ ማሸትንና ማስጨነቅን የሚገልጽ ትዕምርት ነው፡፡[12] የእጆችን መዳፎች እርስበርስ በኃይል ማማታት በቁጥጥር ስር ውሎ የታሸው ቡድን እንዲህ ይመታ! እንዲህ ይውደም! የሚል ትርጉም አለው፡፡

የእጅ ምቱ ለሶስት፣ ለሰባት ወይም ለአስር ጊዜ ሊከወን ይችላል፡፡ የእጅ ምቱ ቁጥር የራሱ ትርጉም አለው፡፡ ሶስት ቁጥር የምሉዕነት ተምሳሌት ነው፡፡ ምቱ ሶስት ጊዜ መሆኑ የተሟላ እርግማን ማድረግን ለማረጋገጥ ነው፡፡ ሰባት ቁጥር የቃልኪዳንና የፍጻሜ ተምሳሌት ነው፡፡ ምቱ ሰባት

---

[9] - አቶ ኑማን ሼኽ መሐሙድ፣ አናጂና ቀበሌ፣ ቃለመጠይቅ፣ መጋቢት 26፣ ቀን 2008 ዓ.ም፡፡

[10] - አቶ ኑማን ሼኽ መሐሙድ እና ሼኽ በክሪ ሼኽ መሃመድ፣ አናጂና ቀበሌ፣ ቃለመጠይቅ፣ መጋቢት 26፣ ቀን 2008 ዓ.ም፡፡

[11] - አቶ ኑማን መሃመድ፣ ሼኽ ዑስማን ከዲር፣ ሼኽ በክሪ ሼኽ መሃመድና አቶ መሃመድ ሼኽ መሃሙድ፣ አናጂና ቀበሌ፣ ቃለመጠይቅ፣ መስከረም 12 ቀን 2008 ዓ.ም፡፡

[12] - ሼኽ ዑስማን ከዲር፣ መሃሙድ፣ አናጂና ቀበሌ፣ ቃለመጠይቅ፣ መስከረም 12 ቀን 2008 ዓ.ም፡፡

ጊዜ መሆኑ በእርግማኑ ምክንያት ለሚወሰድባቸው እርምጃ ውሳኔ መስጠትን የሚገልጽ ቃልኪዳን ነው፡፡ አስር ቁጥር የማይቋረጥ ረጅም ጊዜን የሚወክል ተምሳሌት ነው፡፡ ምቱ ለአስር ጊዜ መሆኑ ደግሞ እርግማኑ ቀጣይ፣ ለረጅም ጊዜ የሚቆይና ለዘለዓለም የጸና መሆኑን ለመግለጽ ነው፡፡ እርግማኑን የሚናገረው የፕሮግራሙ መሪ ሲሆን፣ እሱ ያለውን ሕዝቡ በአንድ ላይ ይደግማል፡፡

አራተኛ፤ እጅን በትንፋሽ መጥረግ ነው፡፡ የፕሮግራም መሪው "አብር" የሚል ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡ ሕዝቡም ወደ ላይ የዘረጋውን የእጅ መዳፍ ሰብሰብ በማድረግ ሁሉም ሰው ውስጥ እጁን በትንፋሹ እፍ-እፍ-እፍ ይላል፡፡ የእጅ መዳፍን በትንፋሽ እፍ-እፍ-እፍ ማለት ማስወገድን፣ መጥረግን ወይም ማባረርን የሚወክል ትዕምርት ነው፡፡ በዚህ ትዕምርት መሰረትም የሚረገመው ቡድን እንዲጠፋ ወይም እንዲወገድ ይደረጋል፡፡ ይህ እርግማን የሚረገመውን አካል ከምድረገጽ የሚያጠፋና የሚያወድም እንደሆነ ይታመናል፡፡

እነዚህ የእርግማን ስርዓተከበራዎች ተከውነው ሲጠናቀቁ የማሳረጊያ ስርዓት ይፈጸማል፡፡ ስርዓቱም ፊርማ ነው፡፡ የፕሮግራም አስተባባሪው የእርግማን ክወናዎችን ሲያጠናቅቁ "ፈርም!" በማለት ሕዝቡን ያዛል፡፡ ሕዝቡም በእጁ መሬት ላይ የመፈረም ምልክት ያሳያል፡፡ ይህ ፊርማ የእርግማኑ ማረጋገጫ ነው፡፡ ውሳኔን ማስተላለፊያ ነው፡፡ የተከፈተን የክስ ፋይል መዝጊያ ነው፡፡ የተሰጠው ቃል እንዳይታጠፍ ማረጋገጫ ማህተም ነው፡፡[13] ይህ የፊርማ ስርዓት የእርግማን ስርዓትን ከመግለጽ በተጨማሪ ወደ ሌላ ክወና መሸጋገርን የሚያሳይ የክወና ቅየሳ ድርጊት ነው፡፡

## የምህላ ስርዓተከበራ

በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነቅርስ የምህላ ስርዓተከበራ የሚከወነው በአገር፣ በክልል፣ በዞን ወይም በመካነቅርሱ አካባቢ ችግር ሲከሰት ነው፡፡ ችግሩ የአገራት ጦርነት፣ የእርስበርስ ግጭት፣ የመንግስትና የሕዝብ ግጭት፣ በሽታ፣ ረሃብ፣ የዝናብ እጥረት ወይም ወረርሽኝ ሊሆን ይችላል፡፡ ሕዝቡም ፈጣሪ ከችግሩ እንዲያወጣቸው፣ ሼኽ ሁሴን ችግሩን እንዲፈቱላቸው ይጸልያሉ፤ ይለምናሉ፡፡

ምህላውን የሚያቀርበው የፕሮግራሙ አስተባባሪ ነው፡፡ ምህላውም በልመና፣ በጥያቄና በትንተና መልክ ይቀርባል፡፡ የፕሮግራሙ አስተባባሪ

---

[13] - አቶ ኑማን መሃመድ፣ ሼኽ ዑስማን ከዲር፣ ሼኽ በክሪ ሼኽ መሃመድ እና አቶ መሃመድ ሼኽ መሃሙድ፣ አናጂና ቀበሌ፣ ቃለመጠይቅ፣ መስከረም 12 ቀን 2008 ዓ.ም፡፡

ምህላውን በጥያቂ መልክና በትንተና መልክ ሲያቀርብ፣ ተመልካቹ "አዎ" በማለት የፕሮግራም መሪውን ምህላ ያጸናል፡፡ የፕሮግራሙ አስተባባሪ ምህላውን በልመና መልክ ሲያቀርብ፣ ተመልካቹ "አሜን" በማለት የፕሮግራም መሪውን ምህላ ያጠናክራል፡፡

በ2009 ዓ.ም በኢድ-አል አድሃ የሙዳ በዓል ወቅት በአገር ደረጃ የተፈጠረውን የሰላም እጦትና በአካባቢው የተከሰተውን የዝናብ እጥረት ስጋት እንዲቀርፍላቸው ለፈጣሪ፣ ለነብዩ መሐመድና ለሼኽ ሁሴን የምህላ ስርዓት ሲከውኑ ተመልክቻለሁ፡፡ ይህ ምህላ በወቅቱ በተለያዩ የአገሪቷ አካባቢዎች በነበረው የዝናብ እጥረት ምክንያት ማሳ ላይ ያለ እህል እየደረቀ፣ ከብቶች እየሞቱ፣ ሰዎች በረሃብ እየተጠቁ በመሆኑ የተከናወነ ነው፡፡

በመካነቅርሱም አካባቢ የዝናብ እጥረት በመኖሩ የውኃ ኩሬዎች እየደረቁ ነበር፡፡ ይህ ወቅት እጅግ አሳሳቢ ነበር፡፡ በመረጃ ስብሰባዬ ወቅት ሕዝቡ ረጅም ሰዓት የፈጀ የዝናብ ልመና ምህላ ካካሄደ በኋላ፣ ሕዝቡ ምህላውን ሳይጨርስ ሰማይ በደመና ተሸፍኖ የተወሰነ ዝናብ ተንጠባጥቦ ተመለሰ፡፡ በዚህ ወቅት  ከሕዝብ ይሰማ የነበረ የደስታ እልልታ ከፍተኛ ነበር፡፡[14]

## የሰርመዴ መንፈሳዊ ሙዚቃ ክወና

የሰርመዴ መንፈሳዊ ሙዚቃ በቡድን በመሆን የሚከወን ነው፡፡ በቡድን ሲከወን አንድ ከዋኝ በተሰበሰበው ሕዝብ መሃል ላይ በመቆም ወይም መሬት በመቀመጥ ክወናውን ያቀርባል፡፡ ታዳሚውም ከዋኙን መሃል በማድረግ፣ በክብ ቅርጽ በመሰባሰብና መሬት ቁጭ በማለት የክወናው ተሳታፊ ይሆናል፡፡ ከዋኙ መንፈሳዊ ሙዚቃውን ሲያቀርብ፣ ታዳሚው የግጥሙን አዝማች በመድገም፣ እንደዜማው ስልት አንገትን ወደ ግራና ወደ ቀኝ በማወዛወዝና ከክወናው አቅራቢ ጋር አብሮ በማዜም ንቁ ተሳታፊ ይሆናል፡፡

የሰርመዴ መንፈሳዊ ሙዚቃ በሁለት መንገድ ይቀርባል፡፡ አንደኛው፣ ያለምንም አይነት የሙዚቃ መሳሪያ ሲሆን፣ ይህ በሙዳ በዓላት ወቅት በዋሬ ስርዓተከበራ ላይ የሚቀርብ ነው፡፡ ሁለተኛው፣ ደግሞ በከበሮና በጭብጨባ የሚከወን ሲሆን፣ ይህ በቤት ውስጥ በሚከወኑ ስርዓቶች

[14] - ይህ ክስተት በመረጃ ስብሰባዬ ወቅት በጣም ካስገረሙኝ ገጠመኞቹ መካከል አንዱ ነው፡፡

ላይ የሚቀርብ ነው፡፡ ነው፡፡ ያለምንም የሙዚቃ መሳሪያ የሚቀርበው የሰርመዴ መንፈሳዊ ሙዚቃው የዋሬ ስርዓተከበራ ሊጠናቀቅ ሲል የሚከወን ነው፡፡ በዋሬ ስርዓተከበራ የጊዜ ቅደም ተከተል መሰረት ከንጋቱ አስር ሰዓት ገደማ ተጀምሮ እስከ ጠዋቱ አስራ ሁለት ሰዓት ድረስ ይከወናል፡፡ አልፎ አልፎም መንፈሳዊ ሙዚቃውን ቀን ላይ ሰዎች በቡድን በቡድን በመሆን ይከውናሉ፡፡

በዋሬ ላይ የሚከወነው የሰርመዴ መንፈሳዊ ሙዚቃ በተረጋጋ ስሜትና ለፈጣሪ በሚደረግ ምልጃ አይነት ዜማ ስላለው፣ ቀልብን የማረጋጋትና ስሜትን በቀላሉ የመንካት ባህርይ አለው፡፡ በዚህም ባህሪው ይመስላል የመንፈሳዊ ሙዚቃው ከዋኝም ሆነ ታዳሚ በጥልቅ ስሜት ውስጥ በመግባት የሚከወነው፡፡

## የዝክሪ ስርዓተከበራ

“ዝክሪ” የሚለው ቃል፣ “ዚክር” ከሚለው የአረብኛ ቃል የመጣ ነው፡፡ ቃሉም ሁለት እሳቤዎችን ይገልጻል (Renard, 2005)፡፡ አንደኛው፤ ፈጣሪን ማስታወስ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ከፈጣሪ ጋር ያለን ግንኙነት የሚገልጽ ነው፡፡ በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነቅርስ የተለያዩ የዝክሪ ስርዓተከበራዎች አሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል የሀጂ አደም ሀድራ፣ የአብሮኜ ዝክሪና ዶውሪን በአጭሩ እንመልከት፡፡

በሐጂ አደም ሀድራ የሚከወን መንፈሳዊ ሙዚቃ ‘ሹቢሳ’ ይባላል፡፡ ሹቢሳ የሚለው ቃል የኦሮምኛ ቃል ሲሆን፣ ትርጉሙም ጭፈራ ማለት ነው፡፡ ይህ መንፈሳዊ ሙዚቃ በደማቅ ጭብጨባና በድቤ (በከበሮ) የታጀበ ነው፡፡ መንፈሳዊ ሙዚቃውም ጭፈራ መሰል የሰውነት እንቅስቃሴም አለው፡፡ የሀድራ ስርዓት የሚከወነው በምሽት ብቻ ነው፤ በቀን አይከወንም፡፡ ሀድራው መከወን የሚጀምረው ከምሽቱ አራት ሰዓት አካባቢ ሲሆን፣ የሚያበቃው ደግሞ ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት ገደማ ነው፡፡ በሐጂ አደም ሀድራ ላይ የሚከወን የሹቢሳ መንፈሳዊ ሙዚቃ አቅራቢ የግጥሙን አዝማች ሲል፣ ታዳሚው አዝማቹን በጋራ ይደግማል፡፡

የአብሮኜ ዝክሪ የሚከወነው ከመካነቅርሱ ዋና መግቢያ በር በግምት ሁለት መቶ ሜትር ርቀት ላይ በሚገኝ ቦታ ነው፡፡ ዝክሪው የሚከወነው በሙዳ በዓል ወቅት ለአንድ ቀን ብቻ በመሆኑ፣ በዓመት ሁለት ጊዜ ብቻ ይከወናል፡፡ የዝክሪው ክወና የሙዳ በዓላት በሚከበሩበት በመጀመሪያው ቀናት ከምሽቱ አምስት እስከስድስት ሰዓት ባለው ጊዜ ተጀምሮ፣ ከሌሊቱ ሰባት ሰዓት እስከሰባት ከሰላሳ ደቂቃ ባለው ጊዜ ውስጥ ይጠናቀቃል፡፡ የአብሮኜ ዝክሪ እሳት በማንደድ የሚከወን ነው፡፡ እሳት ለማንደድ የሚጠቀሙት ወፋፍራም የግራር እንጨቶችን ነው፡፡ እንጨት ማንደድ የሚጀምሩት ከምሽቱ ሶስት ሰዓት አካባቢ ነው፡፡

ክወናው በእሳቱ ዙሪያ ክብ በመሆን መንፈሳዊ ሙዚቃዎችን ማቅረብና የተለያዩ መንፈሳዊ ድርጊቶችን መፈጸምን ይይዛል፡፡

ሀድራውን የሚከውኑት፣ የሚያስፈጽሙትና በእሳቱ የመጀመሪያ ረድፍ ላይ በመሰለፍ ክብ የሚሰሩት የአብሮኜ ጎሳ አባላት ብቻ ናቸው፡፡ ከአብሮኜ ጎሳ አባላት ውጪ ሌላ ማንኛውም ሰው ስርዓቱን አይከውንም፤ በእሳቱ የመጀመሪያ ረድፍ ላይም መሰለፍ አይችልም፡፡ የአብሮኜ ጎሳ ከአርሲ ኦሮሞ አቢይ ጎሳ ስር ከሚካተተው የቡላላ ንዑስ ጎሳ ስር የሚመደብ ነው (የኦሮሚያ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ፣ 1998 ዓ.ም)፡፡ ጎሳው በአርሲ ዞን ገደብና ዲደአ በሚባሉ ቦታዎች እንዲሁም በባሌ ዞን ቆላማ አካባቢዎች በስፋት ይኖራል፡፡

ዝክሪው በሚከወንበት ስፍራ ላይ የተዘጋጀው የግራር እንጨት በደንብ ሲቀጣጠልና ከፍተኛ እሳት መፍጠር ሲጀምር ዝክሪው መከወን ይጀምራል፡፡ እሳት የማቀጣጠል ስርዓት "ዋዚዣ" ወይም "ዋሲሳ" በሚል ስያሜ ይጠራል፡፡ በስፍራውም እሳት በማቀጣጠል የዝክሪ መንፈሳዊ ሙዚቃ ይከወናል፡፡ መንፈሳዊ ሙዚቃው የሚከወነው አንድ ከዋኝ ግጥሞቹን ሲያቀርብ ሌላው ሰው በጋራ የግጥሙን አዝማች በመድገም፣ በማጨብጨብና በእልልታ ያጅቡታል፡፡ የዝክሪው ከዋኞችም ከፊት ለፊት መስመር ወደ መሃል ተራ በተራ በመግባት የተወሰኑት እሳቱን ከቀኝ ወደ ግራ በመዞር መንፈሳዊ ሙዚቃውን ይከውናሉ፡፡

"ዶውሪ" በቡድን በመሰባሰብ ክብ መስራት ማለት ነው፡፡ ዶውሪ የጸሎት ስርዓት ነው፡፡ የዶውሪ ስርዓት በመኖሪያ ቤት ውስጥ የሚከወን ነው፡፡ ይህ ስርዓት ከሌሎች ስርዓቶች ልዩ የሚያደርገው በርካታ ቁጥር ያላቸው ሰዎች በአንድ ቤት ተሰባስበው ጫት እየቃሙ ጸሎት የሚያደርጉበት ሲሆን፣ ምንም ጩኸት፣ መንቀዥቀዥ እንዲሁም ድምጽን በጣም ከፍ አድርጎ ማውራት ፈጽሞ የተከለከለ ነው፡፡ ስርዓቱ እጅግ የተረጋጋና በከፍተኛ የተመስጦ ስሜት የተሞላ እንደሆነ በምልከታ ወቅት ተመልክቻለሁ፡፡

በዶውሪ ወቅት ለሚከወን የጸሎት ክዋኔ ጫት ዋና ግብዓት ነው፡፡ በመካነቅርሱ ጫት መቃም ይበረታታል፡፡ ጫት መቃም ከድካም፣ ከድብርትና ከእንቅልፍ ስሜት ስለሚታደግ ሰዎች ጠንክረው ጸሎት እንዲያደርጉ ያስችላቸዋል ተብሎ ይታመናል፡፡ ዶውሪ ረጅም ሰዓት የሚፈጅ የጸሎት ስርዓት ነው፡፡ በዚህ ረጅም የጸሎት ስርዓት ወቅት ሰዎች ያለመድከምና ያለመሰልቸት ጸሎት እንዲያደርጉ ጫት ከፍተኛ ጥቅም አለው የሚል ዕምነት የዶውሪ ተሳታፊዎች አላቸው፡፡

በዶውሪ ስርዓተከበራ ወቅት ግለሰቦች ተሰባስበው የግላቸውንም ሆነ በአገር ጉዳይ ላይ ጸሎት ያደርጋሉ፡፡ ስርዓቱ ከሰዓት በኋላ ወደ ዘጠኝ

ሰዓት አካባቢ የሚጀመር ሲሆን፣ በአብዛኛው የሚጠናቀቀው ከንጋቱ አስር ሰዓት አካባቢ ነው፡፡ ከእነዚህ ሰዓታት መካከል በእኩለ ሌሊት አካባቢ ያሉ ሰዓታት ልዩ ቦታ ይሰጣቸዋል፡፡ በእነዚህ ሰዓታት የፈጣሪ በር ክፍት እንደሚሆን ይታመናል፡፡ በእነዚህ ሰዓታት ወቅት የሚደረግ ጸሎት፣ ምርቃት ወይም እርግማን የፈጣሪን ፈጣን ምላሽ ያስገኛል ተብሎ ይታመናል፡፡

በዶውሪ ስርዓተከበራ በአብዛኛው የሚከወነው መንፈሳዊ ሙዚቃ ‹አቶረራ› ነው፡፡ የአቶረራ መንፈሳዊ ሙዚቃ ከሌሎች መንፈሳዊ ሙዚቃዎች የተለየ የሚያደርጉት ባህርያት አሉ፡፡ ከእነዚህም ባህርያት መካከል የመንፈሳዊ ሙዚቃው ግጥም ስንኞች በመጨረሻ ፊደላት የተለያዩ በመሆናቸው ግጥሙ ቤት አይመታም፡፡ የግጥሞቹ ይዘትም የተለያዩ ርዕሰጉዳዮችን የሚዳስስ ነው፡፡ ርዕሰጉዳዮቹም ስለፍቅር፣ ስለሀገር፣ ስለተፈጸመላቸው ተዓምራት፣ ስለሰው ልጅ ባህርይ፣ ስለፖለቲካ እንዲሁም ስለራሱ (ስለሚከውነው ግለሰብ) ገጠመኝ የያዙ ናቸው፡፡ በአንድ የአቶረራ መንፈሳዊ ሙዚቃ ውስጥ ከአዝማቹ በስተቀር ሌላው ግጥም አይደገምም፡፡

## በከራ ጉዶ እና በቅጽር ግቢው ውስጥ የሚከወኑ ስርዓተከበራዎች

በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነቅርስ አስር ገሞዎች አሉ፡፡ እነዚህ ገሞዎች በግንብ በታጠረው ቅጽር ግቢ ውስጥና ከቅጽር ግቢው ውጪ የሚገኙ ናቸው፡፡ ከቅጽር ግቢ ውጪ አምስት ገሞዎች የሚገኙ ሲሆን ገሞዎቹም የሼኽ ኢብራሂም መልካይ፣ የአዮ ማኪዳ፣ የሼኽ መሃመድ ቲልማ ቲልሞ፣ የሼኽ መሃመድ ሚስኪ እና የሼኽ መሃመድ ሀጂ አህመድ ናቸው፡፡ በግንብ በታጠረው ቅጽር ግቢ ውስጥ ደግሞ አምስት ገሞዎች፣ የሀሮ ሉኩ የዘምዘም ኩሬ፣ የአዮ ሀደ ገራዶ ጎምቢሶ እና የሼኽ ቡሽራ ጎምቢሶ ይገኛሉ፡፡

ገሞ በኦሮምኛ ህንጻ ማለት ሲሆን ጎንቢሶ፣ ደግሞ አዳራሽ ማለት ነው፡፡ ከእነዚህ ኪነሕንጻዎች በተጨማሪ የመቃብር ስፍራ አለ፡፡ በዚህ ስፍራ የአናጂና ቀበሌ ነዋሪዎች፣ በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነቅርስ መንፈሳዊ ጉዞ ለማድረግ መጥተው ሕይወታቸው እዛው ያለፈ እንዲሁም በተለያዩ ምክንያቶች በስፍራው መንነው የሚኖሩ ሰዎች ከዚህ ምድር በሞት ሲለዩ የሚቀበሩበት ነው፡፡

በሙዳ በዓላት ወቅት በመካነቅርሱ በሚገኘውና በግንብ በታጠረው ቅጽር ግቢ ዋና የመግቢያ በር ላይ እንዲሁም በቅጽር ግቢው ውስጥ በሚገኙ ስፍራዎች የተለያዩ ስርዓተከበራዎች ይከወናሉ፡፡ እነዚህም፤ የግቢውን ዋና የመግቢያ በርንና ገሞዎችን የመሳለም፣ የዘምዘም ጸበል የመጠጣትና ሰውነትን የማሻሸት፣ የጀዋራ ቅዱስ አፈር የመቀባት

እንዲሁም ስለት የመሳል ስርዓተከበራዎች ናቸው፡፡ እነዚህን ስርዓተከበራዎች በአጭሩ እንመልከት፡፡

**የግቢውን ዋና የመግቢያ በር የመሳለም ስርዓት**

መንፈሳዊ ተጓዦች በግንብ ወደታጠረው ግቢ ውስጥ ከመግባታቸው በፊት የመሳለም ስርዓት ይፈጽማሉ፡፡ ከዚህ ስርዓት በኋላ ለስለት ወይም ለስጦታ በሚል ይዘው የሚመጡትን ሰንደልና ጧፍ በመግቢያው በር ይለኩሳሉ፡፡ እጣን፣ ከርቤና ሉባንጃ ጊርጊራ ወይም ከሰል ማንደጃ ላይ በማድረግ ያጨሳሉ፡፡ አልፎ አልፎ ሽቶ የሚረጩም አሉ፡፡

ጭስ የሚያጨሱትና ሽቶ የሚረጩት ስፍራው የተቀደሰ በመሆኑ ልዩ መዐዛ በአካባቢው እንዲኖር ነው፡፡ ከዚህም ባለፈ ሰንደል፣ እጣን፣ ሽቶ ወይም ሌሎች ጥሩ መዐዛ ያላቸውን ነገሮች በአካባቢው ለሚገኝ ቅዱስ መንፈስ መስዋዕት ለማቅረብ ነው፡፡ መስዋዕቱም ለመንፈሶቹ የሚደርሰው በሽታ ነው፡፡ ሽታ የሰው ልጅ ከረቂቅ መንፈስ ጋር ለሚያደርገው ግንኙነት አንዱ የመገናኛ ድልድይ ነው፡፡ ሰንደል፣ እጣን፣ ሽቶና መሰል ቁሶችን በቤተአምልኮዎችና አካባቢያቸው ማጨስ በክርስትና፣ በእስልምና እንዲሁም በሌሎች ኃይማኖቶችና እምነቶች ስርዓተአምልኮ ውስጥ የተለመደ ነው፡፡

**ገሞዎችን የመሳለም ስርዓተከበራ**

መንፈሳዊ ተጓዦች በግንብ ወደታጠረው ግቢ ከገቡ በኋላ ገሞዎችን የመሳለም ስርዓት ይፈጽማሉ፡፡ በቅጽር ግቢው መሃል ላይ እራሱን የቻለና ዙሪያው በግንብ የታጠረ ግቢ ይገኛል፡፡ በዚህ ተጨማሪ የግንብ ቅጽር ውስጥ ሶስት ገሞዎች ይገኛሉ፡፡ ገሞዎቹም የሼኽ ሁሴን እና የልጆቻቸው (የመሐመድ ተማም እና የፋጡማ) ናቸው፡፡ ግቢው መሃል ላይ ከሚገኘው ተጨማሪ ቅጽር ግቢ ውጪ የሼኽ አብዱልቃድር ጀይላኒ እና የሼኽ ዑመር ገሞዎች ይገኛሉ፡፡



ፎቶ፣ 3፤ ዙሪያው በግንብ በታጠረው ቅጽር ግቢ ውስጥ የሚገኘውና በውስጡ የሼኽ ሁሴን እና የልጆቻቸው (የመሐመድ ተማም እና የፋጡማ) ገሞዎች የሚገኙበት ቅጽር ግቢ ውጫዊ ገጽታ። (ፎቶ በአጥኚው)።

በቅጽር ግቢ ውስጥ ከሚገኙ ገሞዎች መካከል መንፈሳዊ ተጓዦች የሚሳለሚቸው የሼኽ ሁሴንን ገሞ እና የሼኽ አብዱልቃድር ጀይላኒን ገሞዎች ነው። መንፈሳዊ ተጓዦች በመጀመሪያ የሚሳለሙት የሼኽ ሁሴንን ገሞ ነው። የሼኽ ሁሴን ገሞ የ383 ዓመት እድሜ እንዳለው ይነገራል። ይህ ገሞ የኪነ-ህንጻ ዲዛይኑ እና ትልቀነቱ በአካባቢው ከሚገኙ ሌሎች ገሞዎች የተለየ ያደርገዋል። ገሞው አርባ አምስት ሜትር ርዝመት፣ ሰላሳ አምስት ሜትር ስፋትና አራት ሜትር ከፍታ እንዳለው በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነቅርስ ባህልና ቱሪዝም ጽህፈት ቤት የቀረበ ሪፖርት (2002 ዓ.ም) ይገልጻል፡፡

መንፈሳዊ ተጓዦቹም በሼኽ ሁሴን ገሞ ውስጥ በመግባት ከቀኝ ወደ ግራ በመዞር ሼኽ ሁሴንን ይዘይራሉ። በሼኽ ሁሴን ገሞ ውስጥ የእሳቸው የመቃብር ስፍራ እንደሆነ በሚታመነውና ቁመቱ በግምት አንድ ሜትር ከፍታ ያለው አራት ማዕዘን ግንብ አለ። እሱን ተሳልመውና ሼኽ ሁሴንን ዘይረው ሲጨርሱ ከገሞው ይወጣሉ። ከገሞው ወደ ውጪ ሲወጡም የራሱ የሆነ የአወጣጥ ስርዓት አለው። ይህም ፊታቸውን ወደ ገሞው ውስጥ በማዞርና ጀርባቸውን ወደ መውጫው በር በማዞር ወደ ኋላ ይወጣል። ከገሞው በጀርባ ተዙሮ ወደ ኋላ የሚወጣበት ምክንያት ለሼኽ ሁሴን ጀርባ መስጠት አይገባም ከሚል አክብሮታዊ አመለካከት ነው።

## የዘምዘም ጸበል የመጠጣትና ሰውነትን የማሻሸት ስርዓተከበራ

በመካነ ቅርሱ ዘጠኝ የውኃ ኩሬዎች ይገኛሉ፡፡ ከእነዚህ የውኃ ኩሬዎች መካከል ለጸበልነት ብቻ የሚያገለግለው የሀሮ ሉኩ የውኃ ኩሬ ሲሆን በግንብ በታጠረው ቅጽር ግቢ ውስጥ ይገኛል፡፡ ይህ ጸበል "ዘምዘም" ተብሎ ይጠራል፡፡ ዘምዘም የአረብኛ ቃል ሲሆን ጸበል የሚል ትርጉም አለው፡፡ የሀሮ ሉኩ የዘምዘም ኩሬ በግምት ሰባት ሜትር ጥልቀትና ሀያ ሜትር በሀያ ሜትር ስፋት እንዳለው የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነቅርስ ባህልና ቱሪዝም ጽህፈት ቤት የቀረበ ሪፖርት (2002 ዓ.ም) ይገልጻል፡፡ ይህን ኩሬ ያስገነቡት ሼኽ ሁሴን እራሳቸው እንደሆኑ ይነገራል፡፡

መንፈሳዊ ተጓዦች ወደ ስፍራው ሲመጡ በሀሮ ሉኩ የዘምዘም ጸበልን ይጠቀማሉ፡፡ ዘምዘም ሰውን፣ እንስሳትንና እጽዋትን ከተለያዩ በሽታዎች ይፈውሳል፤ ከመኖሪያ ቤትና ከአካባቢው ክፉ መናፍስትን ያርቃል፤ በኑሮ ላይ ረድዔትና በረከት ያጎናጽፋል፤ ሕይወትን ስኬታማ ያደርጋል፤ ተብሎ ይታመናል፡፡ በመሆኑም ወደ ስፍራው የሚመጡ መንፈሳዊ ተጓዦች በውኃ መያዣ ጄሪካኖችና የፕላስቲክ ዕቃዎች ዘምዘም በመቅዳት ወደ መኖሪያ ቤታቸው ይወስዳሉ፡፡ ዘምዘሙን በዕቃ ወደ መኖሪያ ቤት ከመውሰድ በተጨማሪ በስፍራው ዘምዘሙን ይጠጣሉ፤ ሰውነታቸውንም ያሻሻሉ፡፡

## የጀዋራ ቅዱስ አፈር የመቀባት ስርዓተከበራ

የሙዳ በዓል ሲቃረብ የጀዋራ አፈር ተቆፍሮ በገሞዎች ውስጥ ይቀመጣል፡፡ በመካነቅርሱ ከሚገኙ ገሞዎች መካከል የጀዋራ አፈር የሚበተነው በሼኽ ሁሴን እና በሼኽ አብዱልቃድር ጀይላኒ ገሞዎች ውስጥ ብቻ ነው፡፡ የጀዋራ አፈርን ለመድኃኒትነት እንዲሆን ያደረጉት በ18ኛው መቶ ክፍለዘመን በስፍራው የተለያዩ ኪነህንጻዎችን ያስገነቡት ሼኽ መሃመድ ቲልማ ቲልሞ እንደሆኑ ይነገራል፡፡ እሳቸውም "ይህ ጀዋራ ለሕመም መፈወሻ፣ ቅዱስ አፈር ይሁን፡፡" ብለው ለፈጣሪ ጸሎት አድርገው፤ ተፈቀደላቸው፡፡ ጸሎታቸው ሲፈቀድላቸው ከቆርቃ ወንዝ ሄደው የጀዋራን አፈር አመጡ፡፡[15] ያመጡትንም አፈር በገሞዎች ውስጥ እንዲቀመጥና ለመድኃኒትነት እንዲያገለግል አደረጉ፡፡[16]

---

[15] - የቆርቃ ወንዝ በመካነቅርሱ ክልል ውስጥ የሚገኝ ሲሆን፣ ከዋናው የግንብ አጥር በደቡብ ምስራቅ አቅጣጫ በግምት 3 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ይገኛል፡፡

[16] - አቶ ኑማን ሼኽ መሃመድ፣ አንጂና ቀበሌ፣ ቃለመጠይቅ፣ ነሐሴ 26 ቀን፣ 2009 ዓ.ም፡፡

ሼኽ መሃመድ የጀዋራ አፈርን በገሞዎች ውስጥ ካደረጉ በኋላ አርባ ጊዜ ቁርዓን ቀሩበት፡፡ ቁርዓንን አርባ ጊዜ ከቀሩ በኋላ ምራቃቸውን በአፈሩ ላይ ተፉበት፡፡ ይህም አፈሩ ለመድኃኒትነት እንዲያገለግልና እንዲቀደስ ነው፡፡ 40 ቁጥር በአምልኮ ሥርዓቱ ፈፃሚዎች ኃይማኖት መሰረት የመስዋዕት፣ የቁርጠኝነት፣ የጸጸት፣ የስቃይ፣ ከአንድ ደረጃ ወደ ሌላ ደረጃ የመሸጋገር፣ የመታደስና የመንጻት ምልክት ነው፡፡

በፈጣሪ ፍቃድ፣ በሼኽ መሃመድ ጸሎት፣ ቁርዓን በመቅራትና በእሳቸው ምራቅ የጀዋራ አፈር ቅዱስ አፈር ሆነ፡፡ ከዛን ጊዜ ጀምሮም የጀዋራ አፈር ቅዱስ አፈር እንደሆነ ይታመንበታል፡፡ ይህ የሼኽ መሐመድ መንፈሳዊ ድርጊት አንድን ቁስ ወደ መለኮታዊ ቁስነት የማሻገር (Cosmological transformation) ሂደት ነው፡፡ በዚህ የሽግግር ሂደት የእሳቸው ምራቅ ለአፈሩ መለኮታዊ ሽግግር ዋና ግብዓት (Cosmic Egg) ነው፡፡ በዚህ የምራቅ ግብዓት አማካኝነት አፈሩ ከነበረው ቀደምት ይዘት፣ ትርጓሜና አገልግሎት በመሻገር ወደ ሌላና አዲስ መንፈሳዊ አገልግሎት ተቀየረ፡፡

አማኞቹ የጀዋራ አፈርን በተለያዩ መንገዶች ይጠቀሙበታል፡፡ ስለሆነም፣ አማኞች ሰውነትን በመቀባት፣ የጀዋራ አፈርን በመብላት፣ የጀዋራን አፈር በዘምዘም ጸበል በመበጥበጥ መጠጣት ወይም ሰውነታቸውን ማሻሸት፣ የጀዋራ አፈርን ወደ መኖሪያ ቤት በመውሰድ ምቹ ቦታ በማስቀመጥ፤ እንዲሁም የጀዋራን አፈር በዘምዘም ጸበል በመበጥበጥ መኖሪያ ቤትን፣ ግቢውን፣ የእንስሳት ማደሪያን፣ እንስሳትን፣ የእህል ጎተራን፣ የምግብ ማብሰያ እቃዎችን፣ የእህል አዝመራን ለመርጨት ይገለገሉበታል፡፡

## ስለት የመሳል ስርዓተከበራ

ግለሰቦች በሕይወታቸው ውስጥ የሚያጋጥሟቸው በርካታ ችግሮች አሉ፡፡ ከእነዚህ ችግሮች መካከል የጤና እክል፣ የሀብት እጦት፣ የደስታ እጦት፣ የልጅ እጦት፣ የበረከት እጦት፣ የማህበራዊ ግንኙነት ችግር የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ፡፡ ግለሰቦቹ በሕይወታቸው ከሚያጋጥሟቸው መሰል ችግሮች ለመዳን ወይም ወደፊት በሕይወታቸው ውስጥ ማሳካት የሚፈልጉትን ነገር ለማግኘት በሼኽ ሁሴን ስም ስለት ይሳላሉ፡፡ ግለሰቦቹም ከደረሰባቸው ችግር ለመዳን ወይም የሚፈልጉትን ለማግኘት ሼኽ ሁሴንን ይለምናሉ፡፡

ስለትን የመሳል ስርዓተከበራ ግለሰቡ እንደሚሳለው ጉዳይ ይለያያል፡፡ የግለሰቡ ችግር፤ የጤና፣ የሀብት፣ የበረከት፣ የሰላም፣ የደስታ የመሳሰሉት ከሆነ በአብዛኛው በሼኽ ሁሴን ገሞ ውስጥ ገብቶ የሼኽ ሁሴንን ገሞ ከተሳለመ በኋላ የእሳቸው የመቃብር ስፍራ እንደሆነ

በሚታመነው አራት ማዕዘን ግንብ ላይ እጁን አሳርፎና ግንባሩን በግንቡ ላይ ደፍቶ የሚፈልገውን ነገር ይጠይቃል፤ ስለት ይሳላል፡፡

የግለሰቡ ችግር፣ የልጅ እጦት ከሆነ የተለየ የመሳል ስርዓተከበራ አለ፡፡ ይኸውም በተለያዩ ምክንያቶች ልጅ መውለድ ያልቻሉ ግለሰቦች፣ ልጅ ለመውለድ አለመቻላቸውንና ስለት እንደሚገቡ ለሚያርፉበት ቤት ባለቤት፣ በዋሬ ላይ ለተሰበሰበው ሕዝብ ይናገራሉ፡፡ ግለሰቡ ለቤቱ ባለቤት የተናገረ ከሆነ ከቤቱ ባለቤት ጋር በመሆን ወደ ሼኽ ሁሴን ገሞ ሄዶ ይመረቃል፡፡ በዚህ ወቅት ግለሰቦቹን የሚመርቀው የቤቱ ባለቤት ነው፡፡ ግለሰቡ ሕዝብ ፊት በዋሬ ላይ የተናገረ ከሆነ፣ በስፍራው ፕሮግራሙን ከሚመሩ ግለሰቦች ጋር በመሆን ወደ ሼኽ ሁሴን ገሞ በመሄድ ይመረቃል፡፡ በዚህ ወቅት ግለሰቦቹን የሚመርቀው የስፍራው ፕሮግራም አስተባባሪ ግለሰብ ነው፡፡

ግለሰቦቹ ከቤቱ ባለቤት ወይም ከፕሮግራሙ መሪ ጋር በመሆን ወደ ሼኽ ሁሴን ገሞ ይሄዳሉ፡፡ በቤቱ ባለቤት ወይም በዋሬ ስርዓት በፕሮግራም መሪ ግለሰቡ ይመረቃል፡፡ የምርቃቱ ሂደትም ግለሰቡ/ግለሰቧ በሼኽ ሁሴን ገሞ ውስጥ ገብቶ መሬት ለይ ከተቀመጠ/ከተቀመጠች በኋላ እግሩን ዘርግቶ/እግሯን ዘርግታ እንዲቀመጥ/እንድትቀመጥ ይደረጋል፡፡ የቤቱ ባለቤት ወይም የፕሮግራሙ መሪ ከሼኽ ሁሴን ገሞ ውስጥ ከተበተነው የጀዋራ አፈር የተወሰነ በእጁ በማንሳት የግለሰቡን/ግለሰቧን ፊት፣ አንገት፣ ትከሻ፣ ደረት፣ ሆድና ጭን ይቀባል፡፡ ግለሰቡ መሬት ላይ በእጅና በእግሩ ጉልበት እንዲንበረከክ/እንድትንበረከክ ይደረጋል፡፡ መራቂውም የግለሰቡን/የግለሰቧን ጀርባ፣ ጭን፣ ሆድና ደረት ጠንከር አድርጎ እያሸ ጸሎት ያደርግለታል/ያደርግላታል፡፡

## በአይናገኜ ገደል የሚከወኑ ስርዓተከበራዎች

የአይናገኜ ገደል ከዋናው የግንብ አጥር በግምት ሶስት ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ይገኛል፡፡ ገደሉ በመካነቅርሱ ሜዳማ ስፍራና ቀጨምሰሬ ተብሎ በሚጠራ ተራራ መሃል ላይ የሚገኝ ነው፡፡ በገደሉ ውስጥ የአይናገኜ ወንዝ ይገኛል፡፡ ሼኽ ሁሴን በዚህ ገደል ውስጥ ከሰው ተሰውረው በዱር ቅጠሎችን እየተመገቡና ጨው በውኃ በጥብጠው እየጠጡ ለአርባ አመታት ያህል በጸሎት ኖረዋል ተብሎ ይታመናል፡፡

ገደል በአረብኛው 'ካውታሃር' ከሚለው ቃል ትርጓሜ ጋር ይቀራረባል፡፡ Smith and Haddad (1981, PP.80) ''በነባር የእስልምና ባህል እሳቤ 'ካውታሃር' ገነት ከመግባት በፊት እራስን የማጽጃ፣ የመቀደሻና ንስኃ የመቀበያ ስፍራ ተደርጎ ይወሰዳል'' በማለት ይገልጻሉ፡፡ በሼኽ ሁሴንም ለአርባ ዓመታት ያህል በአይናገኜ ገደል ውስጥ የኖሩት ወደ ገነት

ከመሄዳቸው በፊት እራሳቸውን ለማጽዳት፣ ለመቀደስና ንስኃን ለመቀበል እንደሆነ ይታመናል፡፡

በአይናገኜ ገደል ርዝመቱ በትክክል የማይታወቅ ዋሻ፣ የኃጢአት ማረጋገጫ መስኮት መሰል ቀዳዳዎች፣ ሼኽ ሁሴን ይሰግዱበት የነበረ ሰፊና ጠፍጣፋ ድንጋይ፣ ሼኽ ሁሴን በስፍራው ጸሎት በሚያደርሱበት ወቅት እሳቸውን ለመብላት የመጡ አውሬዎች ወደ ድንጋይነት እንደተለወጡ የሚታመኑ የእንስሳት ቅርጽ ያላቸው የሚመስሉ ድንጋዮች፣ ሼኽ ሁሴን ረግመዋቸው ወደ ድንጋይነት የተቀየሩ ሰዎች እንደሆኑ የሚታመኑ እና የሰው ቅርጽ ያላቸው የሚመስሉ ድንጋዮች ይገኛሉ፡፡

በሙዳ በዓላት ወቅት መንፈሳዊ ተጓዦች ወደ አይናገኜ ገደል በመሄድ የተለያዩ ስርዓቶችን ይፈጽማሉ፡፡ እነዚህ ስርዓቶች ሶስት ናቸው፡፡ እነሱም፤ በቀዳዳዎቹ ውስጥ መሹለክ፣ በዋሻ ውስጥ የሚገኝ ፈሳሽ ውኃን መጠጣትና ሰውነትን መቀባት፣ እንዲሁም ወደ ገደሉ ውስጥ ጠጠር የመወርወር ስርዓቶች ናቸው፡፡ በአይናገኜ ገደል የሚገኘው ዋሻ ሁለት መግቢያ በሮችና ሁለት መስኮት መሰል ቀዳዳዎች አሉት፡፡ የዋሻው ሁለቱ ቀዳዳዎች የተለያየ መጠን ያላቸውና ጠባቦች ናቸው፡፡ አንደኛው፣ ቀዳዳ በአንጻራዊነት ትንሽ ሰፋ ያለ ሲሆን ሁለተኛው፣ በጣም ጠባብ ነው፡፡

በዋሻው ሁለቱ ቀዳዳዎች መሃል መሹለክ የቻለ ሰው ኃጢአት የሌለበት እንደሆነ ይታመናል፡፡ ኃጢአት ያለበት ሰው በቀዳዳዎቹ መካከል እየሾለከ እያለ፣ ቀዳዳው በራሱ ጊዜ በመጥበብ ያጣብቀዋል፤ ስለሆነም መሹለክ አይችልም ተብሎ ይታመናል፡፡ ይህ መንፈሳዊ ሚት በማህበረሰቡ ዘንድ ከፍተኛ ታማኝነት ስላለው ወደ ስፍራው የሚሄድ ሰው ሁሉ በቀዳዳዎቹ ውስጥ በመሹለክ ከኃጢአት ነጻ ስለመሆኑ ወይም ኃጢአተኛ ስለመሆኑ ማረጋገጫ ይወስዳል፡፡

በቀዳዳዎቹ በመሹለክ ራስን ከኃጢአት ነጻ መሆን ወይም አለመሆንን ከሚፈትኑ ነገሮች መካከል የመሹለኪያው ቀዳዳ ጥበትና የድንጋዩ የማዳለጥ ባህርይ ይጠቀሳሉ፡፡ በቀዳዳዎቹ ውስጥ የመሹለክ ሂደት ከኃጢአት መኖር ወይም አለመኖር ባለፈ የሚሾልከው ግለሰብ ያለውን የአካል ብቃት፣ ትኩረት፣ የመሹለክና ድንጋዩ ሳያዳልጠው የመውረድ ስልትን ማወቅ ይጠበቅበታል፡፡

በአይናገኜ ገደል ውስጥ በግምት ሰላሳ ሜትር ርቀት ጥልቀት ባለው ስፍራ ሰፊና ጠፍጣፋ ድንጋይ አለ፡፡ ይህ ድንጋይ ሼኽ ሁሴን ይሰግዱበት እንደነበር ይነገራል፡፡ መንፈሳዊ ተጓዦች ወደ አይናገኜ ገደል ሲመጡ ድንጋዩ ከሚገኝበት ጥልቀት የተነሳ ይህንን ድንጋይ በእጃቸው

መንካትና እላዩ ላይ መስገድ አይችሉም፡፡ በመሆኑም ከመሬት ጠጠር ያነሱና ጠፍጣፋው መስገጃ ወደሚገኝበት አቅጣጫ ወደ ገደል ይወረውራሉ፡፡ ጠጠር ወደ ገደል ውስጥ የሚወረውሩበት ምክንያትም ወደ ስፍራው በአካል መሄድ ስለማይችሉ፣ በጠጠሩ አማካኝነት ወደ ስፍራው መድረሳቸውን ለመግለጽ ነው፡፡ ጠጠሩ የእነሱ ወካይ ተደርጎ የሚቆጠር በመሆኑም ስፍራው ላይ በአካል እንደደረሱ ይቆጠራል፡፡

በሳዑዲ አረቢያ በሚሄድ የሐጅ መንፈሳዊ ጉዞ ላይ ጠጠር የመወርወር ስርዓት ይፈጸማል፡፡ መንፈሳዊ ተጓዦቹ ጠጠር የሚወረውሩት በፈጣሪ ስም ሰይጣንን እንደሚያወግዙ፣ እንደሚጠሉና የሰይጣንን ምክር እንደማይቀበሉ ለመግለጽ ነው፡፡ በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነቅርስ ድንጋይ የሚወረወረው ሼኽ ሁሴን ወደ ሰገዱበት ስፍራ መድረሳቸውንና እሳቸው በሰገዱበት ድንጋይ ላይ መስገዳቸውን የሚገልጽ ነው፡፡ በመሆኑም የድንጋዩ ተምሳሌት የሳዑዲ አረቢያ-ሚና ድንጋይ ሰይጣንን መምቻ መሳሪያ ሲሆን፤ በድሬ፣ አይናገኜ ገደል ደግሞ ከሼኽ ሁሴን ጋር የመገናኛ መሳሪያ ትዕምርት ነው፡፡ በድንጋዩ አማካኝነት መንፈሳዊ ተጓዦች ከሼኽ ሁሴን የመስገጃ ቦታና ከሼኽ ሁሴን መንፈስ ጋር ይገናኛሉ፡፡

## ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት አቢይ ዓላማ በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነቅርስ የሙዳ ስርዓተከበራ አከዋወን እና ትዕምርት መተንተን ነው፡፡ የሙዳ በዓላት በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነቅርስ በአመት ሁለት ጊዜ የሚከበሩና በመታሰቢያ ስርዓተከበራ ስር የሚካተቱ ናቸው፡፡ ጥናቱ ይዘታዊ ምርምር የጥናት አይነትን የተከተለ ነው፡፡ ጥናቱ ምልከታና ቃለመጠይቅ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን ተግባራዊ ያደረገ ሲሆን፣ የክወና እና ትዕምርታዊ ንድፈሃሳቦችን መሰረት በማድረግ የተዘጋጀ ነው፡፡

በሙዳ በዓላት ወቅት በተለያዩ የአገራችን አካባቢዎች የሚኖሩ የተለያዩ ብሔሮች፣ የውጪ አገር ዜጎች እንዲሁም የእስልምና፣ የክርስትና፣ የዋቄፈና እና የሌሎች ኃይማኖት ተከታዮች ወደ መካነቅርሱ መንፈሳዊ ጉዞ ያደርጋሉ፡፡ መንፈሳዊ ጉዞው በኃይማኖት፣ በጾታ፣ በብሔር፣ በጎሳ፣ በቋንቋ፣ በዜግነት፣ በመደብና በሌሎች ምክንያቶች የተለያዩ ግለሰቦች በጋራ የሚያካሂዱት ነው፡፡ ይህ ልዩ ባህሪውም ለባህልና ለመረጃ ልውውጥ፣ ለእርስበርስ ትውውቅና መከባበር እንዲሁም የአገር አንድነት እሳቤ ለማጎልበት ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡ ይህ ልዩ ባህሪው የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነቅርስ ኢትዮጵያውያንን በአንድ የሚያገናኝ ነው፡፡ ይህ

መሆኑም በልዩነት ውስጥ አንድነትን የሚያንጸባርቅ የአገራችን ልዩ ስፍራ እንደሆነ ጥናቱ ይጠቁማል፡፡

በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነቅርስ በኢድ-አል-አድሃ (አረፋ) እና በገልገላ ጎበና የሙዳ በዓላት ወቅት የተለያዩ ስርዓተከበራዎች ይከወናሉ፡፡ ስርዓተከበራዎቹ በዋናነት የዋሬ፣ በከራ ጉዶ እና በቅጽር ግቢው ውስጥ የሚከወኑ እና በአይናገኜ ገደል የሚከወኑ ስርዓተከበራዎች እንደሆኑ ጥናቱ ያሳያል፡፡ የዋሬ ስርዓተከበራዎች የባሮ መንፈሳዊ ሙዚቃ፣ የሂክማ፣ የአርጆማ፣ ስለት የማስገባት፣ የጪንጫ፣ የምረቃ፣ የእርግማን፣ የምህላ እና የሰርመዴ መንፈሳዊ ሙዚቃ ናቸው፡፡

በቅጥር ግቢው ውስጥ በሚገኙ ስፍራዎች ገሞዎችን የመሳለም፣ የዘምዘም ጸበል የመጠጣትና ሰውነትን የማሻሸት፣ የጀዋራ ቅዱስ አፈር የመቀባት እንዲሁም ስለት የመሳል ስርዓተከበራዎች ይከወናሉ፡፡ በአይናገኜ ገደል የሚከወኑት ደግሞ በዋሻ ቀዳዳዎቹ ውስጥ መሹለክ፣ በዋሻ ውስጥ የሚገኝ ፈሳሽ ውኃን መጠጣትና ሰውነትን መቀባት እንዲሁም ወደ ገደሉ ውስጥ ጠጠር የመወርወር ስርዓቶች ናቸው፡፡

የሙዳ ስርዓተከበራዎች ከማህበራዊና ሀይማኖታዊ ዋጋ አንጻር ልዩ ስፍራ የሚሰጣቸው ክወናዎች እንደሆኑ ጥናቱ አሳይቷል፡፡ ስርዓተከበራዎቹም በቅደምተከተላዊ ስርዓት፣ በተደጋጋሚና በመደበኛነት የሚከወኑ ጠቃሚ ድርጊቶችና ሕዝባዊ ሁነቶች ናቸው፡፡ ጥናቱም እነዚህ ስርዓተከበራዎች ያላቸውን የክወና ቅደምተከተል እና የአከዋወን ስርዓት በተናጠል አመላክቷል፡፡

በሙዳ በዓላት ወቅት የሚከወኑ ስርዓተከበራዎች ለመንፈሳዊ ተጓዦች መንፈሳዊ እሴትን፣ የመንፈስ ለውጥን፣ የምሉዕነት ስሜትንና እርካታን የሚያጎናጽፉ እንደሆኑ ጥናቱ ያሳያል፡፡ የሙዳ ስርዓተከበራዎች የመንፈሳዊ ተጓዦችን፣ የአማኞችንና የከዋኞችን መንፈሳዊ፣ አዕምሯዊና ማህበራዊ ደረጃን ከፍ በማድረግ ከመንፈሳዊ ሀይሎች ጋር ግንኙነት ለመመስረት እንደሚረዱ ጥናቱ አሳይቷል፡፡ ስርዓተከበራዎቹ የማህበረሰቡን ማንነት ለመፍጠር፣ ለመጠበቅና እውቅና ለመስጠት እንደሚያገለግሉ እንዲሁም የእርስበርስ ተግባቦት የሚፈጥሩ መሆናቸውን ጥናቱ አሳይቷል፡፡

## ማጣቀሻ ጽሑፎች

ሰሎሞን ተሾመ፡፡ (2007)፡፡ *ፎክሎር፤ ምንነቱና የጥናቱ የትኩረት አቅጣጫ፡፡* አዲስ አበባ፤ ፋር ኢስት ትሬዲንግ ማተሚያ ቤት፡፡

የኦሮሚያ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ፡፡ (1998)፡፡ *የኦሮሞ ታሪክ፣ እስከ አሥራ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን*፡ (ሁለተኛ አርትኦት)፡፡

የድሬ ሼኽ ሁሴን መካነቅርስ ባህልና ቱሪዝም ጽህፈት ቤት፡፡ (2002)፡፡ *በድሬ ሼኽ ሁሴን መካነቅርስ የሚገኙ ኪነ-ህንጻዎች ታሪክ፡፡* (ያልታተመ ሪፖርት)፡፡

ፈቃደ አዘዘ፡፡ (1991)፡፡ *የሥነ-ቃል መምሪያ፡፡* አዲስ አበባ፤ ቦሌ ማተሚያ ድርጅት፡፡

Bell, C. (1997). *Ritual. Perspectives and Dimensions*. New York: Oxford University Press.

Braukämper, U. (1984). The Islamization of the Arsi-Oromo. In Taddesse Beyene (Ed.), *Proceedings of the Eighth International Conference of Ethiopian Studies*. Addis Abeba: Addis Abeba University Press.

Cooke, B. & Macy, G. (2005). *Christian Symbol and Ritual. An Introduction*. New York: Oxford University Press.

Eliyas Teha. (2012). *Understanding Rituals and Analyzing Songs Performed at Dirre Sheikh Hussein.* (Unpublished Master's Thesis), Department of Social Anthropology, Addis Abeba University.

Eriksen, H. T. (2001). *Small Places, Large Issues: An Introduction to Social and Cultural Anthropology.* ($2^{nd}$ Ed.). London: Pluti Press.

Firth, R. (1967). *Tikopia Ritual and Belief*. Boston: Beacom Press.

Geertz, C. (1973). *Interpritation of Cultures.* New York: Basic Books.

Goldstein, K. (1974). *A Guide for Field Workers in Folklore*. Detroit: Gale Research Company.

Gulevich, T. (2004). *Understanding Islam and Muslim Traditions: An Introduction to the Religious Practices, Celebrations, Festivals, Observances, Beliefs, Folklore, Customs, and Calendar System of the World's Muslim Communities, Including an Overview of Islamic History and Geography*. Michigan: Omnigraphics, Inc.

Jafferson, G. (1978). Sequential Aspect of Story Telling in Conversation. In J. Schenkein (Ed.), *Studies in the Organization of Conversational Interaction.* (pp. 219-248), New York: Academic Press.

Jeylan W. H. (2005). The Functional of African Oral Arts: The Arsi-Oromo Oral Arts in Focus. *African Studies Monographs, 26*(1), 15-58.

Kothari, R. C. (2004). *Research Methodology*. New Delhi: New Age International Publisher.

Punkhurst, A. (1994). Reflections on Pilgrimage in Ethiopia. New Trends in Ethiopian Studies: In Harold G. M. (Ed.), *Proceeding of the $12^{th}$ International Conference of Ethiopian Studies* (pp. 933- 953). New Jersey: Red Sea Press INC.

Rappaport, A. R. (1999). *Ritual and Religion in the Making of Humanity.* Cambridge: Cambridge University Press.
Renard, J. (2009). *The A to Z of Sufism.* Plymouth: The Scarecrow Press.
Salamone, A. F. (Ed.). (2004). *Encyclopedia of Religious Rite, Rituals, and Festivals.* London: Routledge.
Schenchner, R. (2004). *Performance Theory*. London: Routledge.
Smith, J. Haddad, Y. (1981). *The Islamic Understanding of Death and Resurrection*. Albany: State University of New York.
Turner, V. (1967). *The Forest of Symbols: Aspects of Ndembu Ritual.* New York: Cornell University Press.
.